# ሙያዊ ሙዳየ ቃላት

በሥነ-ሕዝብ፣በቤተሰብ እቅድ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣
በአካባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ሳይንስ እንዲሁም
በልማት ላይ ያተኮረ

**በኢትዮጵያ ውስጥ
በጋዜጠኝነት ሙያ ለተሰማሩ የተዘጋጀ**

**በፒ.ኤች.ኢ ኢትዮጵያ የተሰናዳ**



USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

HEALTH POLICY PROJECT

P H E
ETHIOPIA
consortium

© Copyright 2014

PHE Ethiopia Consortium
Phone: + 251-11-663 0833/ + 251-11-663 4121/+ 251-11-663 4116
Fax: + 251-11-663 8127
P.O.Box - 4408 Addis Ababa, Ethiopia.
E-mail: pheethiopia@gmail.org
info@phe-ethiopia.org
www.phe-ethiopia.org

# ሙያዊ ሙዳየ ቃላት

በሥነ-ሕዝብ፣ በቤተሰብ እቅድ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ በአካባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ሳይንስ እንዲሁም በልማት ላይ ያተኮረ

በኢትዮጵያ ውስጥ በጋዜጠኝነት ሙያ ለተሰማሩ የተዘጋጀ


አማካሪ አዘጋጆች

መኩሪያ መካሻ (ረ/ፕሮፌሰር)
ፈቃዱ በሻህ

**Prepaired by**

**Mekuria Mekasha (Assistant professor )**
**Fekadu Beshah**

# ማውጫ
# Contents


1. መግቢያ -------------------- 5
    1.1. የሙያዊ ሙዳየ ቃላት ዝግጅት ሂደት-------------------- 5
    1.1.1. የሙዳየ ቃላት ዝግጅት ሂደት-------------------- 5
    1.1.2. የዘርፍ ባለሙያዎችን አስተያየት ማካተት------------- 6
    1.1.3. ከጋዜጠኞች የተሰጡ አስተያየቶችን ማካተት---------- 6
    1.2. የትርጉም ሥራው ሂደት-------------------- 6

2. የሥነ-ሕዝብ ሙያዊ ሙዳየ ቃላት -------------------- 9
    (Glossary of Population)

3. የቤተሰብ ዕቅድ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና
    ሙያዊ ሙዳየ ቃላት -------------------- 21
    (Glossary of Family Planning and
    Reproductive Health Terms)

4. የአካባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ሳይንስ
    ሞያዊ ሙዳይ ቃላት --------------------37
    (Glossary of Environment and
    Environmental Health Terms)

    4.1. የአካባቢ ቃላት መፍቻ -------------------- 37
    4.2. የአካባቢ ሳይንስ ቃላት መፍቻ ----------- 47

5. የልማት ሙያዊ ሙዳየ ቃላት ------------------ 55
    (Glossary of development terms)

6. List of International Organizations work
    on the area of Health, Environment and
    Development --------------------------------- 59

7. References -------------------- 61

# 1. መግቢያ

ይህ ሙያዊ ሙዳየ ቃላት የተዘጋጀው ጋዜጠኞች በመንግሥት እና በለጋሾች የልማት እና የጤና ሪፖርቶች ላይ እንዲሁም በስነ ሕዝብ እና የአካባቢ ጥበቃ ጽሁፎች ላይ የሚያገኙአቸውን ሙያዊ ቃላት በአግባቡ እንዲረዷቸውና በሪፖርት ሥራቸው ላይም በተሳካ መልክ እንዲጠቀሙባቸው በማሰብ ነው፡፡ሰነዱ በአራት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን፤ የመጀመሪያው የሥነ-ሕዝብ፣ ሁለተኛው የቤተሰብ ክብካቤና የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ ሦስተኛው አካባቢ ጥበቃና አካባቢ ሳይንስ ላይ፣ አራተኛው ደግሞ ልማት ላይ ያተኮሩ ሙያዊ ቃላት ናቸው፡፡

ጋዜጠኞች ሙያዊ የሆኑትን ቃላት ጠንቅቀውና ለይተው ካላወቋቸው እና የአማርኛ አቻ ትርጉሙን ካላገኙት ዘገባቸውን የተዛባ ከማድረጉም በላይ የተደራሻቸውን ግንዛቤም ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንዲያመራ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ይህ ችግር የዘገባውን ጥራት እና የሃሳብን ዝውውር ከማወኩም ሌላ የበርካታ መገናኛ ብዙሃን ችግር እየሆነ ይታያል፡፡ በዚህ የተነሳ በሚፈጠር የዘገባ ጥራት መጓደልም መገናኛ ብዙሃኑ ብቻ ሳይሆኑ አንባቢያንና ተመልካቾች እንዲሁም የዜና ምንጮች ከዘገባ ጥራት መጓደል ጋር ለተያያዙ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡

ይህ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በተወሰኑ ዘርፎች ያሉ እና ጋዜጠኞች በአመዛኙ የሚጠቀሙባቸው ሙያዊ ቃላት የአማርኛ አቻ ትርጉም ጉዳይ በመንግሥት፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በሳይንስ ማህበረሰብ አባላት ዘንድና በአጠቃላይም በመላው ህዝቡ ዘንድ ትኩረትን እያገኙ መጥተዋል፡፡
ለዚህ ችግር የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከትም የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ፣ የጤና እና አካባቢ ጥበቃ ኮንሰርቲየም ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ይሄንን ሙያዊ ሙዳየ ቃላት በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ከዚያም በአማርኛ ተተርጉሞ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

ይህ ህትመት ዋና ዓላማው ያደረገው በተመረጡት አራት ዘርፎች ያሉትን የተወሰኑ ሙያዊ ቃላት ጽንሰ ኃሳብ ለማብራራትና ወጥ የሆነ የአማርኛ ትርጓሜአቸውን ለማስቀመጥ ነው፡፡ በዝግጅቱና በትርጉም ሂደቱ በተቻለ መጠን የየዘርፉ ባለሙያዎች የሚጠቀሙበትንና የሚስማሙበትን ትርጓሜ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡ ፡ ይህ በመደረጉም ጋዜጠኞች በዘገባ ዝግጅት ሂደታቸው የተቃና ሥራ እንዲሰሩ እንደሚያግዛቸው ይታመናል፡፡

ይህ ሙያዊ ሙዳየ ቃላት በአይነቱ የመጀመሪያው በመሆኑ በየጊዜው መሻሻልና መጎልበትን ይፈልጋል፡፡ ይህን በማድረግና ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኞች በሙያዊ ቃላት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማገዝ የሁሉንም የሚመለከታቸውን ወገኖች ትብብርና እገዛ ይጠይቃል፡፡

## 1.1. የሙያዊ ሙዳየ ቃላት ዝግጅት ሂደት

### 1.1.1. የሙዳየ ቃላት ዝግጅት ሂደት

መጀመሪያ ቃላቶቹን የመምረጥና ቃላቱን የማደራጀቱ ሂደት በጣም ፈታኝ ሥራ ነበረ፡፡ ምክንያቱም የአንዳንዶቹ ቃላት ፍቺ በርካታ ጥናትና ንባብን ይጠይቅ ነበርና

ነው፡፡ አዘጋጆቹ መረጃዎችን በማዘጋጀትና የሙያዎቹ ባለቤት የሆኑትን ግለሰቦች ምክር በመጠየቅ እንዲሁም ተገቢነቱንና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ደግሞ ጋዜጠኞችን አነጋግረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህን ሰነድ ለማዘጋጀት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን እና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተዘጋጁ ሰነዶችም ተቃኝተዋል፡፡ በተለያዩ ድርጅቶች የተዘጋጁ የሚዲያ መመሪያዎች ወይም ጋይዶችም የዚሁ የቅኝቱ ሥራ አካል ነበሩ፡ ፡ከተዳሰሱት መካከል የመንግስታቱ ድርጅት ሰነዶች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የኢንተርኔት ምንጮች ይገኙበታል፡፡

## 1.1.2. የየዘርፉ ባለሙያዎችን አስተያየት ማካተት

በተመረጡት አራት ዘርፎች ማለትም በሥነ-ሕዝብ፣ በቤተሰብ ክብካቤና በሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ በአካባቢ ጥበቃና አካባቢ ሳይንስ፣ እንዲሁም ልማት ላይ ባለሙያዎችን ማፈላለግና የሥራው አካል እንዲሆኑ ማድረግ አስቸጋሪነት ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ አስፈላጊነቱን ከተረዱ በኋላ በተለይ በሙያዊ ቃላቱ ትርጓሜ ላይ በሙሉ ፍቃደኝነት እገዛ አድርገዋል፡፡

ከኢንተርኔት ምንጮች የተገኙት ቃላት አንዳንዶቹ በደንብ አልተጻፉም ሌሎቹ ደግሞ ትርጉማቸው ሙሉ ለሙሉ ስህተት መሆኑን ባለሙያዎቹ አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም የባለሙያዎቹ ድጋፍ እነዚህን ትርጓሜዎች በማጥራት በኩል ከፍተኛ እገዛ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለይ ተርጓሚዎቹ ሃሳቡን በደንብ እንድንረዳና እንድንጨብጥ ያደረጉት እገዛ ከፍተኛ ነበረ፡፡

## 1.1.3. ከጋዜጠኞች የተሰጡ አስተያየቶችን ማካተት

የዚህ ሰነድ አዘጋጆች ቃላቱን ለመምረጥና ለማዘጋጀት ያላቸውን የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርትና ተሞክሮ ተጠቅመዋል፡፡ ይሁን እንጂ የጋዜጠኞችን እና የሌሎች በጉዳዩ ላይ መሰል እውቀት ያላቸውን ሰዎች አስተያየት ማካተት በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነበረ፡፡

በመሆኑም በዝግጅቱ ሂደት በተለይ ጋዜጠኞች ዘወትር የምንጠቀምባቸው እነዚህ ናቸው ብለው በመለየቱ በኩል የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡ አንዳንዶቹም በትርጉም ስራ ሂደቱም ከፍተኛ የሆነ እገዛ አድርገዋል፡፡ ከጋዜጠኞች በተጨማሪም የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች የተመረጡት በአመዛኙ ዘገባዎች ተዛቡብን ብለው ወቀሳ የሚያቀርቡ አካላት በመሆናቸው ነው፡፡

## 1.2. የትርጉም ሥራው ሂደት

ሙዳየ ቃላቱ በእንግሊዘኛ ከተዘጋጀ በኋላ ቀጥሎ የተሄደበት የትርጉም ሥራው ነው፡፡ የትርጉም ሥራውን ለማከናወን አዘጋጆቹ የተለያዩ የትርጉም ሥራ ቴክኒካዊ ሂደቶችን ተከትለዋል፡፡ ከተደረጉም ቴክኒካዊ ሥራዎች መካከልም፡-

- የእንግሊዘኛውን ሰነድ ይዘት መተንተን

- የትርጉም ሥራውን ከማከናወን በፊት የቃላትን እና ጽንሰ ኃሳቦችን የመረዳት ሥራ መስራት

- በቃላት ወጥነትና ደረጃ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ

ከዚህም በተጨማሪ የትርጉም ሥራውን ወጥ እና ከሌሎች ሥራዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ለማድረግ የአማርኛ ትርጉም የተሰራባቸውን ሰነዶች የመመልከትና በዚያው ስልት የመሄድ ተግባርም ተከናውኗል፡፡ የትርጉም ሥራውን ጥራት ለማስጠበቅም በትርጉም ሥራ ዘርፍ ተቀባይነት ያላቸው ሦስት ስልቶች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነርሱም፡-

- በተቻለ መጠን ያልተቆራረጠ ወይም ያልተበጣጠሰ የኃሳብ አገላለጽ ያለው የትርጉም ሥራን ማከናወን

- በትርጉም ሥራው ሂደት ውስጥ ስህተቶች ሲፈጠሩ ወዲያውኑ እርማት ማድረግ

- ጥልቅ የሆኑ እርማቶችንና ማስተካከያዎችን በክለሳ የትርጉም ሥራ ወቅት ማከናወን ናቸው፡፡

# 2. የሥነ-ሕዝብ መሠየዊ መዳየ ቃላት
## (Glossary of Population)

### Abortion ratio: የጽንስ መቋረጥ መጠን

The number of abortions per 1,000 women ages 15-49 in a given year.
በአንድ አመት ውስጥ እድሜያቸው ከ15 እስከ 49 ከሚደርስ 1 ሺ ሴቶች ውስጥ የታየ የጽንሰ መቋረጥ መጠን::

### Age-Dependency Ratio: በጥገኝነት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች

The ratio of persons in the ages defined as dependent (under 15 years of age and over 64 years) to persons in the ages defined as economically productive (15-64 years) in a population.
በህብረተሰቡ ውስጥ ጥገኛ ተብለው በተካለሉት (ከ15 ዓመት እድሜ በታች በሆኑት እና ከ64 ዓመት በላይ) ዜጎችና አምራች በሆኑ ዜጎች (ከ15-64 አመት እድሜ) መካከል ያለ መጠን ነው

### Age-Sex Structure: የእድሜ-ፆታ ጥንቅር

It is the composition of a population as determined by the number or proportion of males and females in each age category. The age-sex structure of a population is the cumulative result of past trends in fertility, mortality, and migration. Information on age-sex composition is essential for the description and analysis of many other types of demographic data.
በእያንዳንዱ እድሜ ክልል በወንዶችና በሴቶች ቁጥር መካከል የሚታይ ስብጥር ነው:: የህዝብ የእድሜ-ፆታ ስብጥር ከዚህ ቀደም ተያይዞ የመጣ የውልደት፣ የሞትና የስደት ቀመር ውጤት ነው::የእድሜ-ፆታ የመረጃ ጥንቅር የተለያዩ የስነ-ህዝብ መረጃዎችን ለመተንተን ጠቃሚነቱ የጎላ ነው::

### Aging of Population: የአዋቂዎችና አረጋውያን ቁጥር መጨመር

A process in which the proportions of adults and elderly increase in a population, while the proportions of children and adolescents decrease
በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የአዋቂዎችና አረጋውያን ቁጥር ጨምሮ የወጣቶችና የጎልማሶች ቁጥር ማነስ

### Antenatal Policy: የህዝብ እድገት አቀባ ፖሊሲ

The policy of a government, society, or social group to slow population growth by attempting to limit the number of births
በመንግስት፣ በማህበረሰብ ወይም ሌላ ማህበራዊ ቡድን አዲስ የሚወለዱ ዜጎችን መጠን በመገደብ የህዝብ ቁጥር ዕድገትን ለማዘግየት ሲባል የሚተገበር የቅየዳ ፖሊሲ ነው::

## Birth Control: የወሊድ ቁጥጥር

Practices employed by couples that permit sexual intercourse with reduced likelihood of conception and birth. The term birth control is often used synonymously with such terms as contraception, fertility control, and family planning. But birth control includes abortion to prevent a birth, whereas family planning methods explicitly do not include abortion.
በጥንዶች መሃል ወሲባዊ ግንኙነት ሳይቋረጥ የምናልባታዊ የማርገዝና የመውለድ ሁኔታ የመቀነስ ድርጊት ነው:: የወሊድ ቁጥጥር የተሰኘው ቃል የእርግዝና ቁጥጥርና የቤተሰብ ዕቅድ ከመሳሰሉ ቃላት ጋር በተደጋጋሚ በተለዋጭ ቃልነት ጥቅም ላይ ይውላል:: ይሁን እንጂ የወሊድ ቁጥጥር የሚለው ቃል የጽንስ መቋረጥን ሲያጠቃልል የቤተሰብ ዕቅድ ግን በምንም አይነት የጽንስ መቋረጥን አያካትትም::

## Brain Drain: የምሁራን ፍልሰት

The emigration of a significant proportion of a country's highly skilled, highly educated professional population, usually to other countries offering better economic and social opportunity (for example, physicians leaving a developing country to practice medicine in a developed country).
በከፍተኛ ደረጃ ብዛት ያላቸው የተማሩና ከፍተኛ የሙያ ክህሎት ያላቸው ዜጎች ከአንዲት ሀገር ወደ ሌላ የተሻለ ሀገር የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት (ለምሳሌ ሀኪሞች ከታዳጊ ሀገራት ወደ በለጸጉ ሀገራት በህክምና ሙያ ለማገልገል ሲሄዱ) ሲሉ የሚያደርጉት ስደት ነው::

## Case Fatality Rate: በአንዱ በሽታ ዓይነት የተከሰተ የሞት መጠን

The proportion of persons contracting a disease who die from it during a specified time period
በአንድ ውስን ጊዜ ውስጥ በአንድ የበሽታ ዓይነት ከተያዙ ሰዎች ውስጥ በዚያ በሽታ ሳቢያ የሞቱ ሰዎች ብዛት ነው ::

## Census: የህዝብ ቆጠራ

A canvass of a given area, resulting in an enumeration of the entire population and often the compilation of other demographic, social, and economic information perting to that population at a specific time
በአንድ የተወሰነ አካባቢ የአጠቃላዩን ህዝብ ቁጥር ለማወቅ ሲባል፤ በአብዛኛው በአንድ ወቅት ከህዝቡ ጋር የተያያዘ የስነ-ህዝብ፣የማህበራዊና የኢኮኖሚ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥናት።።

## Childbearing Age: የወሊድ እድሜ

The reproductive age span of women, assumed for statistical purposes to be 15-44 or 15-49 years of age.
ከ15 እስከ 44 ወይም ከ15 እስከ 49 አመት እድሜ ክልል (ሴቶች ልጅ መውለድ የሚችሉበት የእድሜ ክልል)ነው::

**Closed Population:** **ያልተቀየጠ ህዝብ**

A population with no migratory flow either in or out, so that changes in population size occur only through births and deaths.
ሰዎች ከአገር ባለመውጣታቸው ወይንም ሌሎች ሰዎች ወደ አገር ውስጥ ባለመግባታቸው ምክንያት ወጥ የሆነ የህዝብ ብዛት ያለው ሲሆን፤ የህዝብ ብዛቱ የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው እዚያው በሚወለዱና በሚሞቱ ዜጎች ብቻ ነው::

**Completed Fertility Rate:** **በወላድነት የመጨረሻ ዕድሜ የተወለዱ ህጻናት መጠን**

The number of children born per woman to a cohort of women by the end of their childbearing years
በመጨረሻው የወላድነት እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የተወለዱ ህፃናት መጠን

**Consensual Union (Irregular Union) :** **ጋብቻ ሳይኖር አንደባልና ሚስት አብሮ መኖር**

Cohabitation by an unmarried couple for an extended period of time although such unions may be quite stable, they are not regarded as legal marriages in official statistics.
ላልተወሰነ ጊዜ ሳይጋቡ አብረው የሚኖሩ ጥንዶች ሆነው በይፋዊ መረጃ ግን ህጋዊ ጋብቻ እንዳላቸው የማይቆጠሩ::

**Contraceptive Prevalence:** **የእርግዝና መከላከያ ተጠቃሚዎች መጠን**

Percentage of couples currently using a contraceptive method.
የእርግዝና መከላከያ ዘዴን የሚጠቀሙ ጥንዶች በመቶኛ::

**Death Rate:** **የሞት መጠን**

The number of deaths per 1,000 populations in a given year
በአንድ አመት ውስጥ ከ1000 ሰዎች መካከል በሞት የተለዩ ሰዎች ቁጥር::

**Demographic Transition:** **የህዝብ ብዛት ለውጥ**

The historical shift of birth and death rates from high to low levels in a population. The decline of mortality usually precedes the decline in fertility, thus resulting in rapid population growth during the transition period.
በአንድ ህዝብ ታሪክ ውስጥ የውልደትና የሞት መጠን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ መጠን ማሽቆልቆል:: የሞት መጠን መቀነስ ብዙውን ጊዜ ከውልደት መጠን መቀነስ ቀድሞ የሚከሰት በመሆኑ በሽግግር ወቅት ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመርን ያመጣል::

## Demography: ስነ - ህዝብ

The scientific study of human populations, including their sizes, compositions, distributions, densities, growth, and other characteristics, as well as the causes and consequences of changes in these factors
የህዝብ ብዛትን ማለትም መጠኑን፣ ስብጥሩን፣ ስርጭቱን፣ ክምችቱን፣ እድገቱንና ሌሎች ባህርያትን፣እንዲሁም በነዚህ ባህሪያት ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን ምክንያትና ውጤት የሚያጠና ሳይንሳዊ ዘዴ ነው::

## Dependency Ratio: የጥገኝነት መጠን

The ratio of the economically dependent part of the population to the productive part; arbitrarily defined as the ratio of the elderly (ages 65 and older) plus the young (under age 15) to the population in the working ages (ages 15-64).
ምርታማ ከሆነው ህዝብ አንፃር የኢኮኖሚ ጥገኛ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል መጠን የሚያሳይ ሲሆን፤ ቀጥተኛ ትርጉሙ የተያያዘው እድሜያቸው 65ና ከዚያ በላይ የሆኑና ከ15 አመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ከሰራተኛው ሃይል የእድሜ ደረጃ (ከ15-64 አመት እድሜ) አንጻር ያለውን የጥገኝነት መጠንን ያሳያል::

## Depopulation: የህዝብ ብዛት ማሽቆልቆል

The state of population decline.
የህዝብ ብዛት በአሃዝ እያሽቆለቆለ መሄድ::

## Divorce Rate (or crude divorce rate): የፍቺ መጠን

The number of divorces per 1,000 population in a given year
በአንድ አመት ውስጥ ከ1000 ህዝብ የሚሰላ የፍቺ ቁጥር ነው::

## Doubling Time: የሕዝብ ቁጥር የእጥፌታ ጊዜ

The number of years required for the population of an area to double its present size, given the current rate of population growth.
ለአንድ አካባቢ ህዝብ አሁን ካለው የህዝብ ብዛት በእጥፍ ለመጨመር የሚያስፈልገው የአመታት መጠን

## Economic Infrastructure: ምጣኔ - ሀብታዊ መሰረተ - ልማት

Economic infrastructure includes the internal facilities of a country that make business and financial activity possible, such as communication, transportation, and distribution networks; financial institutions and markets; and energy supply systems.
ምጣኔ-ሀብታዊ መሰረተ-ልማት የሚያጠቃልለው አንድ ሀገር ውስጣዊ አቅርቦቷን የምታሟላባቸውን የንግድና የገንዘብ እንቅስቃሴዎች እንዲጎለብቱ የምታደርግበት ሲሆን፤ እነዚህም መገናኛን፣ትራንስፖርትንና የስርጭት ድሮችን፣ የገንዘብ

ተቋማትን፣ ገበያንና የሃይል አቅርቦት ስርአቶችን ሁሉ ያካትታል::

**Economic Security:** ምጣኔ-ሀብታዊ ዋስትና

The condition of having stable income or other resources to support a standard of living now and in the foreseeable future
የኑሮ ደረጃን በወቅቱና በዘላቂነት ለመምራት የሚያስችል የተረጋጋ ገቢ ወይም ሌሎች ምንጮች የመሙአላት ሁኔታ ነው::

**Ethnicity:** ብሄረሰባዊ ማንነት

The cultural practices, language, cuisine, and traditions-not biological or physical differences-used to distinguish groups of people.
የተወሰነ የህዝብ ክፍልን በመወለድ ወይም በቀለም ልዩነት ሳይሆን በባህላዊ፣ በቋንቋ፣ በአመጋገብና በልማዳቸው የመለያ መንገድ ነው።

**Family:** ቤተሰብ

Usually two or more persons living together and related by birth, marriage, or adoption. Families may consist of siblings or other relatives as well as married couples and any children they have.
በአብዛኛው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ሲኖሩና በውልደት፣ በጋብቻ ወይም በጉዲፈቻ የተቆራኙ ሲሆን፤ ቤተሰቦች ዘመዳሞችን ወይም ሌሎች የቅርብ ዘመዶችንና (ወገኖችን) በተጨማሪም የተጋቡ ቤተሰቦችንና ያሉአቸውን ልጆች ያጠቃልላል።

**Fecundity:** መውለድ መቻል

The physiological capacity of a woman to produce a child
አንዲት ሴት ልጅ ለመውለድ ያላት ተፈጥሮአዊ (ስነ-ህይወታዊ) ብቃት::

**Gender Equity:** ጾታዊ ፍትሃዊነት

It is the process of being fair to women and men. To ensure fairness, measures must be taken to compensate for historical and social disadvantages that prevent women and men from operating on a level playing field.
ለሴቶችና ለወንዶች ካለመድልዎ እኩልነትን የማስፈን ሂደት ነው::ፍትሀዊ እኩልነትን ለማስፈን ከዚህ ቀደም የተከሰቱ ታሪካዊና ማህበራዊ ጫናዎችን በማስወገድ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ከመጫወቻ ሜዳዉ የማያገሉአቸውን የማካካሻ ርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል::

**Gender Equality:** ጾታዊ እኩልነት
Is the state or condition that affords women and men equal enjoyment of human rights, socially valued goods, opportunities, and resources
ሴቶችና ወንዶች በጾታቸው ሰብአዊ መብትን፣ማህበራዊ እሴቶችንና ሀብቶችን በእኩልነት የመጠቀም ሁኔታ ነው::

## General Fertility Rate: አጠቃላይ የወላድነት ልኬት

The number of live births per 1,000 women ages 15-44 or 15-49 years in a given year.
በአንድ ዓመት ውስጥ በመውለድ የእድሜ ክልል (ከ15-44 ወይም ከ15-49 እድሜ) ውስጥ ከሚገኙ 1000 ሴቶች በህይወት የተወለዱ ህጻናት ቁጥር::

## Growth Rate: የእድገት ልኬት

The number of people added to (or subtracted from) a population in a year due to natural increase and net migration expressed as a percentage of the population at the beginning of the time period
በተፈጥሮአዊ እደገትና በንጥር የፍልሰት መጠን ምክንያት በነባሩ የህዝብ ብዛት ላይ የተጨመሩ (ወይም የተቀነሱ) ሰዎች ብዛት በመቶኛ ስሌት::

## High-risk pregnancies: ከከባድ አደጋ የተጋለጠ እርግዝና

A high-risk pregnancy is one that threatens the health or life of the mother or her fetus.For most women, early and regular prenatal care promotes a healthy pregnancy and delivery without complications. But some women are at an increased risk for complications even before they get pregnant for a variety of reasons.Risk factors for a high-risk pregnancy can include: Existing health conditions, Overweight and obesity, Multiple births and Young or old maternal age.

ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠ እርግዝና ማለት የእናትየዋን ወይንም የጽንሱን ጤና ወይም ህይወት ስጋት ውስጥ የከተተ እርግዝና ማለት ነው። አብዛኛዎቹ ሴቶች የቅድመ ወሊድ ወቅት የህክምና ክትትልን ቀደም ብለው በመደበኛነት ከተከታተሉ ጤናማ ወሊድ ይፈጽማሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሴቶች ከማርገዛቸው በፊት ሳይቀር በተለያየ ምክንያት ለውስብስብ ችግሮች ይጋለጣሉ። ለአደጋ ወደተጋለጠ እርግዝና ከሚያመሩ ጠንቆች መካከል ነፍሰ-ጡሯ ያላት የጤና ሁኔታ፣ ከፍተኛ ክብደት ወይም ቅጥ ያጣ ውፍረት፣ ተደጋጋሚ ወሊድ እና ለአካለ መጠን ሳይደርሱ ማርገዝ ወይም እድሜ ከገፋ በኋላ ማርገዝ ይገኙበታል።

## Illegal Alien (undocumented alien): ህጋዊነት የሌለው የውጭ ዜጋ

A foreigner who has entered a country without inspection or without proper documents, or who has violated the terms of legal admission to the country, for example, by overstaying the duration of a tourist or student visa.
ወደ አንድ አገር በህጋዊ መልክ ያልገባ፣ ህጋዊ ማስረጃ የሌለው ወይም ህጋዊ የውጭ ሀገር ዜጋን የቅበላ ደንብ የጣሰ የውጭ አገር ሰው ማለት ሲሆን፤ ለምሳሌ ያህል ለቱሪስት ወይም ለተማሪ የተሰጠን የቪዛ የጊዜ ገደብ በማራዘም በአንድ ሃገር ውስጥ የቆየ የውጭ ሀገር ዜጋን ያጠቃልላል::

## Immigration: ፍልሰት

The process of entering one country from another to take up permanent or semi permanent residence
ቋሚ ወይም በከፊል ቋሚ የሆነ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ሲባል ወደ አንድ ሀገር የመግባት ሂደት::

## Immigration Rate: የስደት ልኬት

The number of immigrants arriving at a destination per 1,000 populations at that destination in a given year
በ1000 የህዝብ ብዛት ልኬት መጠን በአንድ ውስን አመት ውስጥ ወደ አንድ ሀገር የደረሱ የስደተኞች ቁጥር::

## Incidence Rate: ከበሽታ የመጋከጥ ልኬት

The number of persons contracting a disease per 1,000 populations at risk, for a given period of time
በአንድ የተወሰነ ጊዜ ለበሽታ ከተጋለጡ ከ1000 ህዝብ ውስጥ በሽታ የያዛቸው ሰዎች ቁጥር::

## Infant Mortality Rate: የጨቅላ ህፃናት ሞት መጠን

The number of deaths of infants under age 1 per 1,000 live births in a given year
በአንድ ውስን አመት ከተወለዱ 1000 ህጻናት ውስጥ ከ1 አመት እድሜ በታች ሆነው የሞቱ ህጻናት ቁጥር::

## In-migration: የሀገር ውስጥ ስደት

The process of entering one administrative subdivision of a country (such as a province or state) from another subdivision to take up residence
ለዘላቂ መኖሪያ ሲባል ከአንድ አስተዳደራዊ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ(ክልል ወይም ክልላዊ መንግስት) ገብቶ የመኖር ሂደት::

## Least Developed Countries: በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት

Following United Nations' definitions, the term "least developed countries" includes 51 countries: Afghanistan, Angola, Bangladesh, Benin, Bhutan, Burkina Faso, Burundi, Cambodia, Cape Verde, Central African Republic, Chad, Comoros, Democratic Republic of the Congo, Djibouti, Equatorial Guinea, Eritrea, Ethiopia, Gambia, Guinea, Guinea-Bissau, Haiti, Kiribati, Laos, Lesotho, Liberia, Madagascar, Malawi, Maldives, Mali, Mauritania, Mozambique, Myanmar, Nepal, Niger, Rwanda, Samoa, São Tomé and Príncipe, Senegal, Sierra Leone, Solomon Islands, Somalia, Sudan, South Sudan,Tanzania, Timor-Leste, Togo, Tuvalu, Uganda, Vanuatu, Yemen,

and Zambia. These countries are also “less developed” in United Nations’ terminology.
የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት ኋላቀር ሀገራት ተብለው የሚታወቁት 51 ሀገራት ናቸው:: እነሱም አፍጋኒስታን፣ አንጎላ፣ባንግላዴሽ፣ ቤኒን ፣ቡታን፣ቡርኪና ፋሶ፣ብሩንዲ፣ካምቦዲያ፣ኬፕ ቨርዴ ፣ማእከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ፣ቻድ፣ኮሞሮስ፣ኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ፣ጂቡቲ፣ኢኩዋቶሪያል ጊኒ፣ኤርትራ፣ኢትዮጵያ፣ ጋምቢያ፣ጊኒ፣ጊኒቢሳኦ፣ ሀይቲ፣ኪሪባቲ፣ላኦስ፣ሌሶቶ፣ላ ይቤሪያ፣ማዳጋስካር፣ማላዊ፣ማልዲቭስ፣ማሊ፣ማውርታኒያ፣ሞዛንቢክ፣ማይንማር ፣ኔፓል፣ኒጀር፣ርዋንዳ፣ሳሞአ፣ሳኦቶሜ እና ፕሪንሲፔ፣ሴኔጋል፣ሴራሊዮን ፣የሰለሞን ዴሴቶች፣ሶማሊያ፣ሱዳን፣ደቡብ ሱዳን፣ታንዛኒያ፣ቲሞር-ሌስቴ፣ቶጎ፣ቱቫሉ፣ኡጋንዳ፣ ቫኑአቱ፣የመንና ዛምቢያ ናቸው::

## Less Developed Countries: ዝቅተኛ አድገት ያላቸው ሀገራት

Following United Nations’ definitions, the term “less developed countries” (or regions) refers to countries in Africa, Asia (except Japan), Latin America and the Caribbean, and Oceania (except Australia and New Zealand).
የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባስቀመጠው ትርጉም መሰረት ዝቅተኛ እድገት ያላቸው ሀገራት(ወይም ክልሎች) የሚባሉት ሀገራት የሚገኙት በአፍሪካ፣በእስያ (ጃፓንን ሳይጨምር)፣ላቲን አሜሪካና የካሪቢያን፣የኦሺያና ሀገራትን(አውስትራሊያንና ኒው ዚላንድን ሳይጨምር) ያጠቃልላል::

## Life Span: በህይወት የመኖር ዘመን

The maximum age that human beings could reach under optimum conditions
የሰው ልጆች በመካከለኛ የኑሮ ሁኔታ በህይወት መኖር የሚችሉበት ከፍተኛው የእድሜ መጠን::

## Life Expectancy: የዕድሜ ጣሪያ

The average number of additional years a person could expect to live if current mortality trends were to continue for the rest of that person’s life. Most commonly cited as life expectancy at birth.
አንድ ሰው የሚጠብቀዉ ማእከላዊ በህይወት የመኖር ተጨማሪ አመታት ብዛት ሲሆን ፣ይህም የወቅቱ የሞት መጠን በሰውየው የህይወት ዘመን የሚቀጥል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡በአብዛኛው የሚጠቀሰው ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ያለው በህይወት የመኖር የጊዜ ገደብ ተደርጎ ነው፡፡

## Male Involvement: የወንዶች ተሳትፎ

Means engaging men in actively promoting gender equity with regard to reproductive health, increases men’s support for women’s reproductive health and children’s well-being, and advances the reproductive health of both men and women.
የወንዶች ተሳትፎ ማለት፣በሴቶች በስነ ተዋልዶ ጤናና በልጆች መልካም የኑሮ ሁኔታ

እንዲሁም የወንድና የሴቶችን የስነ ተዋልዶ ጤናን ለማሻሻል ጾታዊ ፍትሀዊነትን በተሳለጠ መንገድ ለማበረታታት ሲባል ወንዶችን በተጠናከረ መንገድ ማሳተፍ ነው፡፡

## Marriage Rate (or crude marriage rate): የጋብቻ ልኬት

The number of marriages per 1,000 population in a given year.
ከ1000 ሰዎች መካከል በአንድ አመት ውስጥ ጋብቻ የፈጸሙ ሰዎች ብዛት::

## Mean Age: አማካይ እድሜ

The age that divides a population into two numerically equal groups; that is, half the people are younger than this age and half are older.
የሁሉም ዜጎች እድሜ በማእከላዊ የሂሳብ ስሌት ተሰልቶ ሲቀመጥ:: ይህ ዕደሜ ህዝቡን ለሁለት የሚከፍል ሲሆን ግማሽ ያህሉ ከዚህ እደሜ በታች እና ገሚሱ ደግሞ ከዚህ ዕድሜ በላይ የሆናሉ::

## Metropolitan Area: የከተማ ክልል

A large concentration of population, usually an area with 100,000 or more people. The area typically includes an important city with 50,000 or more inhabitants and the administrative areas bordering the city that are socially and economically integrated with it.
ብዙ ህዝብ የተከማቸበትና ከ100,000 ወይም ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የሚኖሩበት ክልል ነው:: በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የተቆራኘ 50,000 ወይም ከዚያ በላይ ነዋሪዎችንና አስተዳደራዊ ክፍልን ያካለለ ከተማን ያጠቃልላል::

## Morbidity: የጉዳት መጠን

The frequency of disease, illness, injuries, and disabilities in a population
በህዝብ ላይ በተደጋጋሚ የሚደርስ የበሽታ፣ የህመም፣የመቁሰልና የአካል ጉዳት::

## More Developed Countries: አጅግ የበለፀጉ ወይም በኢንዱስትሪ ያደጉ ሀገራት

Following United Nations' definitions, "more developed countries," or industrialized countries (or regions), include Europe (including all of Russia), the United States, Canada, Australia, New Zealand, and Japan.
በተባበሩት መንግስታት ትርጉም መሰረት "እጅግ የበለጸጉ ሀገራት" ወይም በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገራት (ወይም ክልሎች) አውሮፓን (መላዋን ሩሲያን ጨምሮ)፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒው ዚላንድን እና ጃፓንን ያካተተ ነው፡፡

## Mortality: የሞት መጠን

Deaths as a component of population change.
እንደ አንድ የስነ-ህዝብ የለውጥ አካል የሚደርስ የሞት መጠን::

## Net Migration: ንጥር ስደት

The net effect of immigration and emigration on an area's population in a given time period, expressed as an increase or decrease.
በአንድ ውስን ጊዜ ውስጥ ፍልሰት (ወደ ውስጥ ወይም ወደ ውጪ) በአንድ ክልላዊ ህዝብ ላይ የሚያደርሰው ንጥር ተፅእኖ በቁጥር መጨመር ወይም በመቀነስ ሲገለፅ::

## Net Reproductive Rate (NRR): ንጥር የተዋልዶ ልኬት

The average number of daughters that would be born to a woman (or a group of women) if she passed through her lifetime conforming to the age-specific fertility and mortality rates of a given year. This rate is similar to the gross reproduction rate but takes into account that some women will die before completing their childbearing years. An NRR of one means that each generation of mothers is having exactly enough daughters to replace itself in the population.
አንዲት እናት (ወይም እናቶች) በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የወለደችው አማካይ የሴት ልጆች ቁጥርን ይወክላል:: ይህ ልኬት ከምሉእ የተዋልዶ ልኬት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፤ አንዳንድ ሴቶች የወሊድ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ የሚሞቱ መሆናቸውን ግምት ውስጥ ያስገባል:: ንጥር የተዋልዶ ልኬት እያንዳንዷዋ እናት በህብረተሰቡ ውስጥ ራስዋን የመተካትና በቂ ሴት ልጆችን የማፍራት መንገድ ማለት ነው::

## Out-migration: ከአካባቢ ለቆ መሰፈር

The process of leaving one subdivision of a country to take up residence in another
ከአንድ የመኖሪያ አካባቢ ለቆ ወደ ሌላ አካባቢ ሰፍሮ የመኖር ሂደት ነው::

## Parity: የእናቶች ወሊድ

The number of children previously born alive to a woman; for example, 'two-parity women' are women who have had two children and 'zero-parity women' have had no live births.
አንዲት ሴት ቀደም ሲል በህይወት የወለደቻቸው የልጆች ቁጥር ነው:: ለምሳሌ ያህል "ሁለት ወለድ" ሲባል ሁለት ልጆች ያላት እናት ማለት ሲሆን "አልቦ ወለድ" ሲባል ደግሞ በህይወት የተወለደ ልጅ የሌላት እናት ማለት ነው::

## Parental Mortality Rate: ቅድመ ወሊድ የሞት ልኬት

The number of fetal deaths after 28 weeks of pregnancy (late fetal deaths) plus the number of deaths to infants under 7 days of age per 1,000 live births.
ከ28 ሳምንታት እርግዝና በኋላ የሞቱትን ቁጥር የሚያሳይ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከ1000 ከተወለዱ ህጻናት መካከል በሰባት ቀናቸው የሞቱትንም ያጠቃልላል::

## Population Control: የህዝብ ብዛት ቁጥጥር

A broad concept that addresses the relationship between fertility, mortality, and migration, but is most commonly used to refer to efforts to slow population growth through action to lower fertility. It should not be confused with family planning. See also family planning.
በወሊድ፣ በሞትና በስደት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ሰፊ ትርጉም የያዘ ሲሆን፤ በአብዛኛው ግን የህዝብ ብዛት እድገትን ለመቆጣጠር የወሊድ መጠንን በመቀነስ ይገለጻል::ቃሉ ከቤተሰብ እቅድ ጋር እንዳይምታታ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

## Population Increase: የህዝብ ብዛት መጨመር

The total population increase resulting from the interaction of births, deaths, and migration in a population in a given period of time.
በአንድ ውስን ጊዜ ውስጥ የአጠቃላይ የህዝቡ ብዛት ከወሊድ፣ ከሞትና ከስደት ጋር በተያያዘ መጨመር ማለት ነው::

## Population Projection: የህዝብ ብዛት ትንበያ

Computation of future changes in population numbers, given certain assumptions about future trends in the rates of fertility, mortality, and migration. Demographers often issue low, medium, and high projections of the same population, based on different assumptions of how these rates will change in the future.
ወደፊት በህዝብ ብዛት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ለውጥ በማስመልከት ከወሊድ፣ ከሞትና ከስደት ጋር አያይዞ መጪውን ሁኔታ የማሳያ መንገድ ነው:: የስነህዝብ ተንታኞች የህዝብ ብዛትን በሚመለከት ዝቅተኛ መካከለኛና ከፍተኛ በማለት መለኪያ በማስቀመጥ ወደፊትም ይህ አሃዝ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ግምት ያስቀምጣሉ::

## Prevalence Rate: የበሽታ የስርጭት ልኬት

The number of people having a particular disease at a given point in time per 1,000 population at risk.
ለአደጋ ከተጋለጡ ሰዎች መካከል በአንድ በተወሰነ ወቅት ከ1000 ህዝብ ልኬት ውስጥ በአንድ በተወሰነ በሽታ የተጠቁ ሰዎች መጠን::

## Purchasing Power: የመግዛት አቅም

The ability of consumers to acquire goods and services based on their possession of money and/or their recourse to credit.
ሸማቾች በያዙት ገንዘብ መጠን ወይም የመበደር አቅም ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን የመግዛት ችሎታ::

## Rate of Natural Increase (or Decrease): ተፈጥሮአዊ የህዝብ ብዛት መጨመር ልኬት

The rate at which a population is increasing (or decreasing) in a given year due to a surplus (or deficit) of births over deaths, expressed as a percentage of the base population.
በአንድ ውስን አመት በትርፍ (ወይም በጉድለት)የሚወለዱ ህፃናት በሚሞቱ ህጻናት ተካፍለው ከመደበኛ የህዝብ ብዛት ከመቶኛ የህዝብ ብዛት መጨመር(ወይም መቀነስ) ሲገለፅ::

**Replacement- Level Fertility:** ራስን የመተካት የወሊድ ደረጃ

The level of fertility at which a couple has only enough children to replace themselves, or about two children per couple.
የጋብቻ ተጉዋዳኞች ራሳቸውን በበቂ የመተካት የወሊድ ደረጃ ወይም አንድ ጥንድ ተጉዋዳኞች ሁለት ልጆችን የመውለድ መጠን::

**Sex Ratio:** ፆታዊ ጥመርታ

The number of males per 100 females in a population
ከነዋሪው ህዝብ መሃል በ100 ሴቶች ልኬት የወንዶች ቁጥር ጥመርታ::

**Social Mobility:** ማህበራዊ የኑሮ ደረጃ ለውጥ

A change in status (for example, an occupational change)
የማህበራዊ ደረጃ ለውጥ ሲባል ለምሳሌ ያህል የስራ አይነት ለውጥ ሊሆን ይችላል::

**Stable Population:** ለውጥ የማያሳይ የህዝብ ብዛት

A population with an unchanging rate of growth and an unchanging age composition as a result of age-specific birth and death rates that have remained constant over a sufficient period of time.
የማይለዋወጥ የህዝብ ብዛት እድገትና የእድሜ ጥንቅር በቂ ለሆነ ጊዜ ተረጋግቶ ሲቀጥል::

**Sustainable Development:** ዘላቂነት ያለው ዕድገት

Development that meets the needs of the present without compromising the ability of future generations to meet their own needs
የወቅቱን ፍላጎት ያሟላ እድገት ሆኖ፤ የወደፊቱ ትውልድ የራሱን ፍላጎት የሚያሟላበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያላስገባ የዕድገት ዓይነት ነው::

**Urban:** ከተማ

Countries differ in the way they classify population as 'urban' or 'rural.' Typically, a community or settlement with a population of 2,000 or more is considered urban.
ሀገሮች የህዝብ ብዛትን "ከተማ" ወይም "ገጠር" ብለው ይለያያሉ::ከ2000 ህዝብ በላይ ያለው ማህበረሰብ ወይም ህዝብ የሰፈረበት ስፍራ ከተማ ተደርጎ ይወሰዳል::

## Urbanization: የከተማነት መስፋፋት

Urbanization Refers to the increasing number of people that live in urban areas. It predominantly results in the physical growth of urban areas, be it horizontal or vertical.
በከተማ አካባቢ የሚኖር ህዝብ ቁጥር መጨመር ሲሆን፤ የከተማው ስፋትም እንደዚሁ ይጨምራል::

## Women's Empowerment: ሴቶችን ማብቃት

Means improving the status of women to enhance their decision making capacity at all levels, especially as it relates to their sexuality and reproductive health.
በሁሉም ደረጃ ሴቶች ውሳኔ የመስጠት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማስቻል ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ ከፆታና ከስነ ተዋልዶ ጤናቸው ጋር በተያያዘ የመብቃታቸውን ሁኔታ የሚመለከት ነው::

## "Yong" Population: የወጣት የህዝብ ክፍል

A population with a relatively high proportion of children, adolescents, and young adults; a low median age; and thus a high growth potential.
በህዝቡ ውስጥ ህፃናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች ከህዝቡ ብዛት አንፃር ከፍተኛውን ቁጥር ሲይዙ::

## Youth: ወጣት

Young people ages 15 to 24.
እድሜያቸው ከ15 እስከ 24 እድሜ ክልል ያሉ ዜጎች ናቸው::

# 3. የቤተሰብ ዕቅድ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና ሙያዊ ሙዳየ ቃላት
## (Glossary of Family Planning and Reproductive Health Terms)

### Abortion: ጽንስ ማቋረጥ

Termination of pregnancy (expulsion or extraction of an embryo/fetus) before 22 weeks gestation or when the fetus weighs less than 500 grams. Abortion may be spontaneous-due to natural causes such as miscarriage- or induced.
ጽንስን ማቋረጥ በእርጉዝ እናቶች ማህጸን ውስጥ ያለን ጽንስ ማስወጣት ወይም እድገቱ እንዲቋረጥ ማድረግ ሲሆን፤ ይህም የሚፈጸመው ጽንሱ 22 ሳምንታት ሳይሞላው ወይንም ክብደቱ ከ500 ግራም ከመብለጡ በፊት ነው። የጽንስ መቋረጥ በመጨንገፍና በህመም ምክንያት ሳይታሰብ ሊከሰት ወይም ሆን ተብሎ ሊቋረጥ ይችላል።

### Abstinence: መታቀብ

Refraining from sexual intercourse
የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ መታቀብ

### Adolescence: አፍላ ወጣትነት

The transition between puberty and adulthood, generally defined as ages 10 to 19.
ይህ ጊዜ ለአካለ መጠን በመድረሻ እና በጎልማሳነት እድሜ መካከል ያለ ሲሆን፤ ይህም እድሜያቸው ከ10 እስከ 19 ያሉትን ያጠቃልላል

### Acquired immune deficiency syndrome (AIDS): ኤድስ

A progressive, usually fatal condition that reduces the body's ability to fight certain infections. It is caused by infection with human immunodeficiency virus (HIV). There is no cure for AIDS, but antiretroviral therapy (ART) can control symptoms and extend life, often for many years
የሰው አካል በተፈጥሮ ያለውን በሽታን የመከላከል አቅም የሚያዳክምና ለተለያዩ ተጓዳኝ በሽታዎች የሚያጋልጥ ሲሆን በአብዛኛው ኤች አይ ቪ በሚባለው ቫይረስ አማካኝነት የሚከሰት በሽታ ነው። ኤድስ እስከ አሁን ፈዋሽ መድሃኒት ባይገኝለትም የፀረ- ኤች አይ ቪ መድሃኒት የበሽታን ምልክቶች በመቆጣጠር ዕድሜ ለማራዘም ይረዳል::

### Amenorrhea: የወር አበባ መቅረት

The absence of menstruation
የወር አበባ መቅረት::

**Andrologist: የወንዶች መካንነት ምርመራ ባለሙያ**

A physician-scientist who performs laboratory evaluations of male fertility. May hold a Ph.D. degree instead of an M.D
የህክምና ሳይንቲስት ሆኖ የወንዶችን መካን መሆንና አለመሆን በላቦራቶሪ ጥናት የሚያረጋግጥ ባለሙያ። ይህ/ች ባለሙያ በአመዛኙ የህክምና ዲግሪ ሳይሆን የፒኤችዲ ዲግሪ ያላት/ ያለው ነው::

**Antenatal period: የእርግዝና ጊዜ**

The period from conception until the onset of labor, approximately 40 weeks
ይህ ጊዜ ጽንሱ ከተጸነሰበት እስከ ምጥ ድረስ ያለውን ጊዜ ሲያጠቃልል፤ በአማካኝ 40 ሳምንታት ይሸፍናል::

**Antiretroviral treatment (ART): ፀረ ቫይረስ ህክምና**

A substance or combination of substances used to destroy a retrovirus (for example, the human immunodeficiency virus, HIV) or suppress its replication.
አንድ ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን፤ እንደ ኤች አይ ቪ አይነት የተለየ ተፈጥሮ ያላቸውን የቫይረስ ዝርያዎች ለማጥፋት ወይም የመባዛት ሂደታቸውን ለመግታት የሚያገለግል ህክምና ነው::

**Artificial insemination: በሰው ሰራሽ ዘዴ የዘር ፍሬን በማህጸን ውስጥ ማስቀመጥ**

The injection of semen into a woman's uterus (not through sexual intercourse) in order to make her pregnant
የወንድን የዘር ፍሬ በሴቷ የመራቢያ አካል ውስጥ በመጨመር እርግዝና እንዲፈጠር ማድረግ (ያለግብረ-ሥጋ ግንኙነት)::

**Assisted Reproductive Technology: ያለ ግብረሥጋ ግንኙነት የማስጸነስ ዘዴ**

Various procedures used to bring about conception without sexual intercourse
ያለ ግብረ-ሥጋ ግንኙነት የማስጸነሻ የተለያዩ ዘዴዎች

**Caesarean Section (Caesarean delivery): በቀዶ ህክምና ማዋለድ**

Removal of the baby and placenta through a surgical cut in the abdominal and uterine walls.
የሆድ እና የማህጸን ግድግዳን በቀዶ ህክምና አማካኝነት በመቅደድ ልጅ ማዋለድ::

**Childbearing years: የወላድነት ዕድሜ**

The reproductive age span of women, assumed for statistical purposes to be ages 15 to 49.
ለስታስቲክስ መረጃ አገልግሎት የተከለለ የሴት ልጅ ጽንስ ለመጸነስ የመቻያ እድሜ ክልል ሲሆን፤ ይህም ከ15 እስከ 49 ያለውን የዕድሜ ክልል ያጠቃልላል::

**Circumcision (male)**: **የወንድ ግርዛት**

Removal of the foreskin or prepuce of the penis
ከወንዱ ብልት ጫፍ ላይ የሚገኘን ስጋ በመቁረጥ የሚደረግ የወንድ ልጅ ግርዛት::

**Chlamydia**: **ክላሚዲያ**

Chlamydia is the most common bacterial STI. If left untreated, it causes pelvic inflammatory disease which can lead to infertility and ectopic pregenancey.
በብዛት የሚከሰት በባክቴሪያ የሚመጣ የአባላዘር በሽታ አይነት ነው። በሽታውን በተገቢው ጊዜ ሳይታከሙ ከቆዩ የመራቢያ አካላት ህመም ያመጣል። ይህም መካንነትንና ከማህፀን ውጪ እርግዝናን ያስከትላል።

**Clean delivery**: **ንጽህና ማዋለድ**

Clean delivery is attended by health staff in a medical institution or by a trained birth attendant at home observing principles of cleanliness, including clean hands, clean surface, and clean cutting of the umbilical cord.
በንጽህና ማዋለድ ማለት ነፍሰጡርን ሴት በጤና ባለሙያዎች ክትትል በጤና ተቋማት ውስጥ ወይንም በሰለጠኑ አዋላጆች አማካኝነት በቤት ውስጥ በንጽህና የማዋለድ ሂደት ሲሆን፤ ይህም በንጹህ እጅ፣ በንጹህ የማዋለጃ ስፍራ እና በንጹህ መቁረጫ እትብት መቁረጥን ያጠቃልላል::

**Clitoridectomy:** **ቂንጥር መቁረጥ**

Removal of part or the entire clitoris
የሴት ልጅን ቂንጥር(ስሜት ቀስቃሽ የሴት ብልት አካል) በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ በመቁረጥ ማስወገድ::

**Contraceptive prevalence rate:** **የእርግዝና መከላከያ የሚወስዱ ሴቶች መጠን**

The percentage of married women of reproductive age (usually ages 15 to 49) currently uses a contraceptive method.
ያገቡና በመውለድ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች (ከ15 እስከ 49 ዓመት) ሆነው በአሁኑ ጊዜ የእርግዝና መከላከያ የሚወስዱ ሴቶች መጠን

**"Date" rape:** **አስገድዶ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸም**

When one person forces another person to have sex. It differs from rape

because the victim agreed to spend time with the attacker. Perhaps he or she even went out with his or her attacker more than once.
አስገድዶ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ሲሆን ይሄ አስገድዶ መድፈር ከሌላው አስገድዶ መድፈር የሚለየው ተጠቂዋ ወይም ተጠቂው ከአስገዳጇ ወይም አስገዳጁ ጋር አብሮ ጊዜ ለማሳለፍ ተስማምቷል። ምንአልባትም ተጠቂዋ/ው ከአጥቂው ጋር ከአንድ ጊዜ በላይ አብረው ወጥተዋል።

**Domestic violence**: **በቤት ውስጥ የሚፈጸም ጥቃት**

Violence that occurs within a family or an intimate relationship, including wife beating and child abuse
በቤተሰቡ አባል ወይንም የቅርብ ወዳጅነት ባለው ሰው አማካኝነት የሚፈጸም ጥቃት ሲሆን፤ ይህም ሚስትን መደብደብንና ልጆችን ማሰቃየትን ያጠቃልላል::

**Dual protection**: **ጥምር የመከላከያ ስልት**

Using two types of contraceptive methods, a barrier method such as a condom and another method such as pills or intrauterine devices, to provide a simultaneous safeguard against both pregnancy and sexually transmitted infections (STIs), particularly HIV
እንደ ኮንደምና የወሊድ መከላከያ እንክብል ወይም ሌላ ሁለት ዓይነት የመከላከያ ዘዴዎችን በጥምር በመጠቀም በአስተማማኝ ሁኔታ እርግዝናን መከላከል ሲሆን፤ ይህም እርግዝናን፤ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ምክንያት የሚፈጠሩ የአባላዘር በሽታዎችንና ኤችአይቪን ለመከላከል ይረዳል::

**Dilation and curettage**: **በመከስተኛ ቀዩ ጥገና ፅንስን ማቋረጥ**

Uses mechanical dilators to open the cervix and metal instruments (curettes) to scrape the uterine walls. The procedure is usually performed under heavy sedation or general anesthesia and has a higher risk of complications. WHO advises that D&C be used only when vacuum aspiration or medication abortion is unavailable.
ይህ ዘዴ ወደ ማኅፀን በሚገባ ብረት ነክ መሳሪያ የማሕፀን በርን በመክፈት በውስጡ ያለውን ነገር በመጥረግ የሚፈፀም የፅንስ ማቋረጥ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በከፍተኛ ጥንቃቄ ማደንዘዣ በመስጠት የሚፈፀም ሲሆን እንደ ዓለም የጤና ድርጅት ምክር ከሆነ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዘዴዎች በማይገኙበት ሁኔታ አገልግሎት ላይ ይውላል።

**Eclampsia and pre-eclampsia**: **ኢክላምሲያና ቅድመ ኢክላምሲያ**

Complications of pregnancy. Pre-eclampsia generally appears in the second half of pregnancy and is marked by high blood pressure, swelling in the hands, legs, and feet, and high protein levels in the urine. It can progress to eclampsia, which can cause convulsions and coma and can be fatal
በእርግዝና ወቅት የሚፈጠር ውስብስብ የህመም ሁኔታ ነው። ቅድመ ኢክላምሲያ

በአብዛኛው በሁለተኛው ግማሽ የእርግዝና ወቅት በከፍተኛ የደም ግፊት፣የእግርና የእጅ ማበጥና በሽንት ውስጥ ከፍተኛ ፕሮቲን ሲገኝ የሚፈጠር የጤና ዕክል ሲሆን ወደ ኢክላምሲያ ደረጃ ሊደርስ ይችላል። ኢክላምሲያ ደረጃ ሲደርስ የሰውነት ማንቀጥቀጥና መገተር (ኮንቨልሽን) እና ራስን መሳት (ኮማ) ብሎም ሞት ሊያስከት ይችላል።

**Ectopic pregnancy**: ከማህጸን ውጪ እርግዝና

Pregnancy outside of the uterus; a life-threatening condition that can cause massive internal bleeding or spontaneous abortion. The pregnancy must be surgically terminated.
ከማህጸን ውጪ የሚከሰት እርግዝና ሲሆን፤ ለህይወት አስጊ በሆነ ደረጃ ከፍተኛ የውስጥ ደም መፍሰስ ወይም ያልታሰበ ውርጃን ሊያስከትል ይችላል። የዚህ ዓይነት እርግዝና ከተከሰተ ጽንሱ የግድ በቀዶ ህክምና መወገድ ይገባዋል።

**Emergency contraception (EC)**: የድንገተኛ ግዜ ወሊድ መከላከያ

Methods used to prevent pregnancy after unprotected intercourse, such as when a contraceptive fails or when sex occurs without contraception. Two types of EC are emergency contraceptive pills (ECPs) and emergency copper-bearing IUD insertion. Both methods are safe and effective if service delivery guidelines and patient instructions are followed correctly.
የተደረገው የመከላከያ መንገድ በትክክል ሳይሰራ ሲቀር ወይንም ያለምንም መከላከያ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በሚደረግበት ወቅት እርግዝናን ለመከላከል የሚወሰድ የመከላከያ ዘዴ ነው። በእንክብል መልክና በማኅጸን በመጨመር የሚሰጡ ሁለት ዓይነት የድንገተኛ ጊዜ የወሊድ መከላከያ መንገዶች ያሉ ሲሆን፤ በአግባቡ ከተወሰዱ ሁለቱም እርግዝናን በመከላከል ረገድ ውጤታማ ናቸው።

**Exclusive breastfeeding**: ውሱን ጡት ማጥባት

Feeding of an infant within one hour of birth until age 6 months exclusively with breast milk and no other fluid or food (not even water)
ጨቅላው ከተወለደ ከአንድ ሰዓት ጀምሮ ስድስት ወር እስኪሞላው ድረስ የእናቱን ጡት ብቻ መመገብ ማለት ሲሆን፤ ከጡት ውጪ ውሃን ጨምሮ ሌሎች ፈሳሾችን ወይንም ምግብ ለህጻኑ አለመስጠትን ያጠቃልላል።

**Family planning**: የቤተሰብ ዕቅድ

The conscious effort of couples to regulate the number and spacing of births through artificial and natural methods of contraception. Family planning usually implies preventing conception to avoid pregnancy and abortion, but it also includes efforts of couples to become pregnant.
የወሊድ ቁጥርን ወይንም አራርቆ የመውለድን ሁኔታ በተፈጥሮአዊ መንገድ ወይም መከላከያ በመውሰድ በግንዛቤ ላይ በተመሰረተ መልኩ የሚደረግ የጥንዶች ጥረት ነው። የቤተሰብ ዕቅድ እርግዝናን ወይንም ውርጃን ማስቀረትን የሚያመላክት ሲሆን፤ ጥንዶቹ እርግዝና እንዲከሰት የሚያደርጉትን ጥረትም ያጠቃልላል።

**Female genital cutting (FfGC)**: የሴት ልጅ ግርዛት

All procedures involving cutting away all or part of the external female genitalia or other injury to the female genital organs whether for cultural, religious, or other nontherapeutic reasons. There are different types of FGC. In the first, the clitoris is partly or completely removed. In the second, the clitoris along with small skin folds of the outer genitals is removed. In the third type, infibulations, the outside genitals are cut away and the vagina is sewn shut, with only a small hole left through which urine and blood can pass.
የሴት ልጅ ግርዛት በባህል፣ በኃይማኖት ወይም ለህክምና ባልሆነ ሌላ ምክንያት በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ የሴቷን የውጪኛውን የብልት አካል ቆርጦ ማስወገድ ወይም የሴት ብልት ላይ ቁስለት የሚያስከትልን ሌላ ድርጊትን የመፈጸም ሂደት ነው። የተለያዩ አይነት የሴት ልጅ ግርዛት አይነቶች ያሉ ሲሆን፤ አንደኛው ቂንጥርን በከፊል ወይንም ሙሉ ለሙሉ ቆርጦ ማስወገድ ነው:: ሁለተኛው መንገድ ቂንጥሩንና በዙሪያው ያለውን አነስተኛ ስጋ ቆርጦ ማስወገድ ሲሆን፤ ሶስተኛው የብልቱን የተወሰነውን ክፍል ከውስጥ ቆርጦ አስወግዶ በተጨማሪ ብልቱን ለሽንት እና ለደም መፍሰሻ ብቻ በመተው መስፋት ነው።

**Fertility**: ዘር ማፍራት

The actual reproductive performance of an individual, a couple.
የአንድ ግለሰብ ወይንም የጥንዶች ዘር የማፍራት ሂደት::

**Fertility Treatment**: አርግዝና እንዲፈጠር የሚደረግ ህክምና

Any method or procedure used to enhance fertility or increase the likelihood of pregnancy.
ማንኛውም የዘር ማፍራት ሂደት እንዲፈጠር ወይም የመጸነስ ሁኔታ እንዲጨምር የሚሰጥ የህክምና ዘዴ::

**Fistula**: ፊስቱላ

An abnormal opening between two cavities (vagina/bladder or vagina/rectum) that can lead to incontinence (inability to retain urine and/or feces)
በሁለት የሰውነት አካላት መካከል ማለትም በብልትና በፊኛ ወይንም በብልትና የሰውነት የቆሻሻ ማስወገጃ አካል መካከል የሚፈጸም ጤናማ ያልሆነ መከፈት::

**Genital herpes**: የብልት አካባቢ ኪንታሮት (ዋርት)

Is a highly contagious infection that is easly transmited between sexual partners and can also be passed from a mother to her baby.
በከፍተኛ ሁኔታ ተላላፊ የሆነና በወሲብ ጓደኞች መሀከል እና ከእናት ወደ ልጅ በጣም በቀላሉ የሚተላለፍ በሽታ ነው።

**Gonorrhea**: ጨብጥ

A sexually transmitted infection caused by the bacterium Neisseria gonorrhoea. It is a common cause of urethral and vaginal discharge and of discharging eyes in newborns. During pregnancy, gonorrhea infections can cause premature labor and stillbirth. Gonorrhea does not have symptoms in all women and, if left untreated, can lead to pelvic inflammatory disease and infertility.
በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚመጣና ኒሴሪያ ጎኖሪያ በተሰኘ ባክቴሪያ አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። በአመዛኙ የወንድ ልጅን የሽንትና የዘር ፍሬ መተላለፊያ ቱቦ እና የሴት ልጅን ብልት የሚያጠቃ ሲሆን፤ በበሽታው ከተጠቃች እናት የሚወለድን ጨቅላ ህጻን አይን እስከማጥፋትም ይደርሳል። ጨብጥ በእርግዝና ወቅት ያለወቅቱ የመውለድ ችግር ወይንም መጨንገፍ ሊያስከትል ይችላል። በሽታው በሁሉም ሴቶች ላይ የመያዝ ምልክት ላያሳይ ይችላል። ነገር ግን የህክምና ክትትል ካልተደረገለት ለአከርካሪ ህመም እና ለመካንነት ያጋልጣል።

**Hemorrhage**: ደም መፍሰስ

Heavy bleeding, the leading cause of maternal death worldwide
ከወሊድ በኋላ የሚደርስ ከፍተኛ ደም መፍሰስ ሲሆን በዓለም ዙሪያ ለእናቶች ሞት አንዱ ምክንያት ነው።

**Human immunodeficiency virus (HIV)**: ኤች አይ ቪ

A virus that attacks the body's immune system, making the body unable to fight infection. It can lead to AIDS, which is the last stage of HIV infection. Because there is no cure, HIV is the most dangerous sexually transmitted infection.
ኤች አይ ቪ ማለት በሽታ ተከላካይ የሆኑ የሰውነት ተሕዋሳትን በማጥቃት ቀስ በቀስ የሰውነትን በሽታ መከላከል አቅም አዳክሞ ለሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎች የሚያጋልጥ የሰውን ልጅ ብቻ የሚይዝ ቫይረስ ነው።

**Hymen**: ድንግልና

Hymen is a membrane that partly covers the entrance to the vagina in most women. It is often ruptured when sexual intercourse takes place for the first time.
የሴቶችን የብልት በር በከፊል የሚሸፍን ስስና ጠንካራ ሽፋን ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ ሲፈፀሙ ብዙ ጊዜ የመቀደድና የመድማት ባህሪ አለው።ይህም በብዙሃኑ ዘንድ የድንግልና ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል።

**Incomplete abortion**: ያልተጠናቀቀ ጽንስ መቋረጥ

An abortion whereby any products of conception remain in the uterus
ጽንስን የማቋረጥ ሂደት ሆኖ፤ ጽንሱ ሙሉ ለሙሉ ሳይወጣ የተወሰነው ክፍሉ በማህጸን ውስጥ ሲቀር።

**Induced abortion**: ሆን ተብሎ የሚደረግ የጽንስ ማቋረጥ

The act of ending a pregnancy with surgery or medicine
በቀዶ ህክምና ወይም መድሃኒት በመውሰድ እርግዝናን ማቋረጥ፡፡

**Infant mortality rate (IMR)**: የሕጻናት ሞት መጠን

The number of deaths of infants under age 1 per 1,000 live births in a given year
በዓመቱ ውስጥ በህይወት ከተወለዱ 1,000 ህጻናት መካከል አንድ ዓመት ሳይሞላቸው የሞቱ ህጻናት ቁጥር

**Incidence rate**: አዲስ በበሽታ የመያዝ ሁኔታ

A measure of the frequency with which a disease occurs in a particular time frame; for example, the number of people who are newly infected with HIV within one year per 1,000 people at risk.
ከ 1000 ሰዎች መካከል በአመት ጊዜ ውስጥ በተለያዩ በሽታዎች አዲስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር

**Intimate partner violence (IPV)**: በቅርብ ወዳጅ የሚደርስ ጥቃት

Defined as actual or threatened physical or sexual violence, or psychological or emotional abuse by a spouse, ex-spouse, boyfriend, girlfriend, ex-boyfriend, or ex-girlfriend
በማስፈራራት ወይም ድርጊቱን በማከናወን የሚፈጸም የወሲብ ወይም የስነ-ልቦና ወይም የስሜት ጥቃት ሲሆን፤ በአመዛኙም በባል ወይም በሚስት፣ በቀድሞ ባል ወይም በቀድሞ ሚስት፣ በሴት ወይም በወንድ ጓደኛ፣ በቀድሞ የወንድ ወይም የሴት ጓደኛ የሚፈጸም ነው፡፡

**Infertility**: መካንነት

Referes to the inability of women or couples to ever have conceived a pregenancy
መካንነት በሴቶች ወይንም በጥንዶች ላይ የሚከሰት እስከመጨረሻው ልጅ ያለመውለድ ችግር ነው፡፡

**Informed choice**: በመረጃ ላይ የተመሰረተ ምርጫ

An individual's ability to choose freely a contraceptive method or medical procedure, or adopt other health behaviors based on accurate and useful information and an understanding of her or his own needs.
ግለሰቦች ትክክለኛና ጠቃሚ የሆነ መረጃ እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ በመረጃ ላይ በተመረኮዘ መልኩና በነጻነት የሚፈልጉትን የእርግዝና መከላከያ፣ የህክምና አገልግሎት ወይም ሌላ ከጤና ጋር የተያያዘ ባህሪይ ለመተግበር የሚመርጡበት መንገድ ነው፡፡

**Integrated services**: የተቀናጀ አገልግሎት

Availability of multiple health services, For example, family planning and STI treatment through a single facility also implies a degree of coordination across services.
በአንድ የህክምና ተቋም ውስጥ የበርካታ ዓይነት የጤና አገልግሎቶች ተሟልቶ መገኘት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትና የአባላዘር በሽታዎች ህክምና በሁሉም የጤና አገልግሎት ክፍሎች ውስጥ በተጣመረ መልኩ ሲሰጥ፡፡

**Labia Majora and Labia minora**: የላይኛው እና የታችኛው የሴት ብልት ከንፈሮች

Labia Majora and Labia minoa surround the opening of the vagina.
የላይኛው እና የታችኛው የሴት ብልት ከንፈሮች የሴት ብልት መግቢያ በርንና የሽንት ቧንቧን የሚሸፍኑ ናቸው፡፡

**Lactational amenorrhea method (LAM)**: ጡት በማጥባት እርግዝናን የመከላከያ መንገድ

A family planning method that relies on breastfeeding as natural protection against pregnancy for up to six months after childbirth. Women who use LAM must fully breastfeed or nearly fully breastfeed to protect themselves from pregnancy.
እናቶች ልጅ ከወለዱ በኋላ እስከ ስድስት ወር ጊዜ ድረስ ጡት በማጥባት ብቻ እርግዝናን የመከላከያ ተፈጥሮአዊ መንገድ ነው፡፡ የዚህን አይነት የመከላከያ መንገድ የሚጠቀሙ እናቶች ራሳቸውን ከእርግዝና ለመጠበቅ ሙሉ ለሙሉ ጡት ማጥባት አለባቸው፡፡

**Live birth**: በህይወት መወለድ

Complete expulsion or extraction of a baby from its mother, irrespective of the duration of the pregnancy, which after such separation breathes or shows other evidence of life such as beating of the heart.
የመወለጃ ወቅቱ ደርሶም ይሁን ሳይደርስ ህጻኑ ከእናቱ ማህጸን በህይወት መወለድ ሲሆን፤ ህጻኑ ከተወለደም በኋላ መተንፈስ ወይም ሌላ የህይወት ምልክት ለምሳሌ የልብ ምት ማሳየት የኖርበታል፡፡

**Low birth weight**: በዝቅተኛ ክብደት መወለድ

The weight at birth is less than 2,500 grams.
ህጻኑ በወሊድ ወቅት ከ2,500 ግራም በታች ከመዘነ በዝቅተኛ ክብደት የተወለደ ህጻን ይባላል፡፡

**Manual vacuum aspiration**: ማንዋል ቫኪዩም አስፓይሬሽን

MVA is performed with the use of a handheld syringe as a source of suction

for removing uterine contents. The procedure time is 5–15 minutes and is performed in settings such as a doctor's office, clinic or emergency room. Providers may use ultrasound to confirm that a woman is pregnant or that the MVA was successful.
ይህ ዘዴ ፅንስን በመሳሪያ በመምጠጥ ለማቋጥ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ሥራ የሚከናወነው በሃኪሞች ቢሮ፣ በክሊኒክና በድንገተኛ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ አገልግሎቱን የሰጡት ባለሙያዎች ጽንሱ አለመኖሩንና የማቋረጥ ሥራውም ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የአልትራ ሳውንድ ምርመራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

## Maternal morbidity: የእናቶች ህመም/ስቃይ

Illness or disability occurring as a result of or in relation to pregnancy, childbirth, or in the postpartum period
በእርግዝና፣ በወሊድ ወይም በአራስነት ወቅት በእርግዝና ወይም ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ምክንያት በእናቶች ላይ የሚደርስ ህመምና ስቃይ፡፡

## Maternal mortality rate: የእናቶች ሞት ልኬት

The number of women who die while pregnant or during the first 42 days following delivery per 100,000 women of reproductive age in a given year for any cause related to or aggravated by pregnancy, but not from accidental or incidental causes.
በአንድ ዓመት ውስጥ በመውለጃ የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ 1 ሺ ሴቶች ውስጥ በእርግዝና ምክንያት ወይንም በወለዱ በ42 ቀናት ውስጥ የሞቱ ሴቶች መጠን ማለት ሲሆን፤ ይህም በአደጋና ሌሎች ከወሊድ ጋር በማይያያዝ ሁኔታ የሞቱትን አይጨምርም፡፡

## Maternal mortality: የእናቶች ሞት

The death of a woman while pregnant, during delivery, or within 42 days (six weeks) of termination of pregnancy. The cause of death is always related to or aggravated by the pregnancy or its management; it does not include accidental or incidental causes.
በእርግዝና፣ በወሊድ ወይም በአራስነት ጊዜ የሚከሰት የእናቶች ሞት ማለት ነው፡ ፡ የሞቱ ምክንያትም የግድ ከእርግዝና ጋር የተያያዘ ወይንም ለእርግዝና ወይንም ለማዋለድ ከሚሰጥ አገልግሎት ጋር መያያዝ አለበት፡፡

## Medication abortion: በህክምና ፅንስን ማቋረጥ

Uses one or more drugs, most commonly mifepristone (known as RU486) and misoprostol (also known as Cytotec), to expel the contents of the uterus. The procedure usually requires at least two outpatient visits and the abortion is almost always complete within a week. In the 2 percent to 5 percent of cases where abortion is incomplete, vacuum aspiration or dilation and curettage is required.
ይህ ዘዴ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያህል ወደ ሃኪም ዘንድ መቅረብ ያስፈልገዋል፡፡ በሐኪም

ትዕዛዝ በሚሰጡ እንደ ሚፌፕሪስቶንና ሚሶፕሮስቶል የሚባሉ መድሃኒቶችን በመውሰድ በአንድ ሳምንት ውስጥ ፅንስን የማቋረጥ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ከሚጠቀሙት ውስጥ ከ 2- 5 በመቶ ያህሉ ያልተሟላ ፅንስ ማቋረጥ ስለሚያጋጥማቸው ወደ ሃኪም ዘንድ ቀርቦ በሌሎች የፅንስ ማቋረጫ ዘዴዎች ዕርዳታ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

**Modern contraceptive methods**: **ዘመናዊ የመከላከያ ዘዴዎች**

Include hormonal methods such as injectables like Depo-Provera, birth control pills and hormonal inplants
ንጥረ ቅመማዊ (ሆርሞናል) ዘዴዎችን ያካተተ በመርፌ የሚሰጥ መከላከያን፣የሚዋጥ እንክብል እና በክንድ የሚቀበር የእርግዝና መከላከያ እንዲሁም የሴትና የወንድ ቋሚ የእርግዝና መከላከያን፣ ሉፕና ሌሎች የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠቃልላል፡፡

**Neonatal death rate**: **የጨቅላ ህጻናት ሞት መጠን**

The number of deaths in the first 28 days of life per 1,000 live births in a given year
በአንድ ዓመት ውስጥ በህይወት ከተወለዱ 1 ሺ ህጻናት መካከል በተወለዱ በ28 ቀናት ውስጥ የሞቱ ጨቅላ ህጻናት መጠን፡፡

**Obstetric emergency**: **የእርግዝና ወይም የወሊድ ወቅድ ድንገተኛ የጤና ችግር**

A severe, life-threatening condition related to pregnancy or delivery that requires urgent medical intervention (emergency obstetric care) to prevent the likely death of the woman. It can occur any time during a pregnancy or up to six months after childbirth and occur suddenly without warning. The woman must be taken to a hospital or health facility without delay.
በእርግዝና ወይም ከምጥ ጋር በተያያዘ በሚከሰት ከፍተኛና ለሞት የሚያሰጋ ህመም ምክንያት የሴቶችን ህይወት ለመታደግ የሚሰጥ አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አደጋ በማንኛውም የእርግዝና ወቅት ወይም ከወለዱ በኋላ እስከ ስድስት ወር ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከሰት ድንገተኛ ህመም ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ህመምተኛዋ ያለምንም መዘግየት ወደ ጤና ተቋም መወሰድ አለባት፡፡

**Pelvic inflammatory disease (PID)**: **ከእንብርት በታችና የማኅፀን አካባቢ ህመም**

A progressive infection that harms a woman's reproductive system. It can occur throughout the pelvic area, fallopian tubes, uterus, uterine lining, and ovaries. PID can lead to infertility (sterility), ectopic pregnancy, chronic pain, and death.
በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ሳይታከሙ ቀርተው ቀስ በቀስ ማህፀን አካባቢና የመራቢያ አካላት ማለትም ማህፀንን፣ የማኅፀን ቧንቧ፣ የማህፀን ግድግዳንና የሴትን እንቁላል ከረጢት ሲጎዱ የሚደርስ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ መካንነትን፣ከማህጸን ውጪ እርግዝናንና ከፍተኛ ህመምን እና ሞት ሊያስከትል ይችላል፡፡

**Post-abortion care**: ድህረ-ፅንስ ማቋረጥ ክብካቤ

Includes emergency treatment of incomplete abortion and potentially life-threatening complications as well as post-abortion family planning counseling and services
ባልተሟላ ፅንስ ማቋረጥ ምክንያት እስከ ሞት የሚደርስን የጤና እክልንና የድህረ-ፅንስ ማቋረጥ የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎትን ጨምሮ የሚሰጥ ህክምና ነው፡፡

**Prenatal death**: መጨንገፍ/መጥፋት

Death of a fetus occurring between the time a fetus weighs at least 500 grams (or after 22 completed weeks of gestation) and the seventh day after the birth of a live-born infant
ጽንሱ በማህጸን ውስጥ ክብደቱ 500 ግራም ከሞላው በኋላ (ከ22 ሳምንታት እርግዝና በኋላ) ወይም በህይወት በተወለደ በሰባት ቀናት ውስጥ የሚከሰት ሞት፡፡

**Postpartum period**: የአራስነት ጊዜ

After childbirth; the period from the delivery of the placenta through the first 42 days after delivery
ከወሊድ በኋላ ያለ የአራስነት ጊዜ ሲሆን፤ ይህም ህጻኑ ከማህጸን ከወጣበት እስከ 42ኛ ቀን ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡

**Prevalence rate**: የበሽታ ስርጭት መጠን

The number of people having a particular disease at a given point in time per 1,000 population at risk
ለበሽታው ከተጋለጡ 1 ሺ ሰዎች መካከል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በበሽታው የተጠቁ ሰዎች ብዛት፡፡

**Reproductive health**: የሥነ-ተዋልዶ ጤና

Reproductive health is a state of complete physical, mental, and social well-being and not merely the absence of disease or infirmity, in all matters relating to the reproductive system and to its functions and processes.
የበሽታ እና ህመም አለመኖር ብቻ ሳይሆን ከተዋልዶ ሥርዓት እና ከዚሁ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሁኔታዎች ጋር በተያየዘ የሚኖር የተሟላ የአካል፣ የአዕምሮ እና ማህበራዊ ደህንነት መኖር ማለት ነው፡፡

**Reproductive tract infection (RTI)**: የተዋልዶ አካላት ህመም

A general term that includes sexually transmitted infections, infections caused by an overgrowth of organisms normally present in the genital tract, and infections acquired during improperly performed medical procedures.
የተዋልዶ አካላት ህመም፣ በአባላዘር በሽታዎች ከተገቢው ቁጥር በላይ በተባዙ

በሰውነታችን ውስጥ በሚገኙ በሽታ አምጪ ባልሆኑ ተሕዋስያን (በተገቢዉ ቁጥር ሲኖሩ በሽታን አያስከትሉም) ወይም ጥንቃቄ በጎደለው ህክምና ምክንያት የሚከሰት ህመም ነው።

**Habitual Abortion**፡ **ተደጋጋሚ ውርጃ**

Repeat miscarriages
ጽንሱ ከማደጉ በፊት የሚፈጠር ተደጋጋሚ ውርጃ።

**Safe motherhood**: **አስተማማኝ የጤና አገልግሎት ለእናቶች**

The goal of safe motherhood is to ensure that every woman has access to a full range of high-quality, affordable sexual and reproductive health services, especially maternal care and treatment of obstetric emergencies to reduce death and disability.
የእናቶች አስተማማኝ የጤና አገልግሎት ዋና ዓላማው እያንዳንዷ ሴት ሙሉ ለሙሉ ከፍተኛ ጥራት ያለውና እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ የእናቶች እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ሲሆን፤ ይህም በተለይ ደግሞ የእናቶችን ሞትና ህመም ለመቀነስ የሚያስችለውን የእርግዝና ወይም የወሊድ ወቅት ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግን ያጠቃልላል።

**Sexually transmitted infection (STI)**: **በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ የአባላዘር በሽታ**

Any infection acquired through sexual contact in a substantial number of cases.
ማንኛውም ከግብረ-ሥጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሚከሰት በሽታ የአባላዘር በሽታ ይባላል።

**Skilled birth attendant**: **የሰለጠነ/ች አዋላጅ**

Refers exclusively to people such as doctors, nurses, and midwives who have been trained to proficiency in the skills necessary to manage normal deliveries and diagnose, manage, or refer complications of pregnancy and delivery.
የሰለጠነ አዋላጅ የሚባሉት ሀኪሞች፣ ነርሶችና ሚድዋይቭስ/አዋላጆችን ብቻ የሚመለከት ነው። እነዚህም በምጥ በማዋለድ፣ ከእርግዝና ጋር የተያያዙ በሽታዎችን በምርመራ የማግኘት፣ የማከም እና ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲከሰትም ወደሚቀጥለውና ከፍተኛው የህክምና ተቋም በመምራት(ሪፈር በማድረግ) ሙያ የሰለጠኑና ብቃት ያላቸው ሙያተኞች ናቸው።

**Stillbirth**: **ሞቶ የተወለደ ልጅ**

Definition of this term varies by country; however, for the purposes of international comparison, the World Health Organization defines stillbirth as a baby born with no signs of life at or after 28 weeks' gestation.

ከማህፀን ሙሉ በሙሉ ሳይወጣ ወይም እንደተወለደ ወዲያውኑ ምንም ዓይነት የህይወት ምልክት ሳያሳይ የተወለደ ልጅ፡፡

**Spontaneous abortion**: ያልታሰበ ውርጃ

Miscarriage or loss of a pregnancy due to natural causes
ሳይታሰብ በተፈጥሮ ምክንያት እርግዝና ሲቋረጥ፡፡

**Syphilis**: ባንቡሌ

Is a genital ulcer disease, which untreated can cause damage to the nervous system, heart or brain and ultimately death. In pregenant women, the infection greately increases the risk of stillbirth and birth defects, making it critical to test for syphilis early in pregenancy.
የብልት መቁሰልን የሚያመጣ የአባላዘር በሽታ ነው፡፡ በተገቢው ጊዜ ካልታከሙት የነርቭ ስርዓትን፣ ልብን ወይም አዕምሮን በማጥቃት ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡ ፡ ይህ በሽታ በእርጉዝ እናቶች ላይ ከተከሰተ ህይወት የሌለው ልጅ መውለድንና በተወለዱት ልጆች ላይም ተጽዕኖ የሚፈጥር ጉዳትን ሊያመጣ ይችላል፡፡

**Total fertility rate**: አጠቃላይ የልጅ ብዛት ምጣኔ

The average number of children that a woman would have assuming that the current age-specific fertility rates remain constant throughout her childbearing years
አንዲት ሴት እስከ መውለጃ ዕድሜዋ መጨረሻ በህይወት ብትቆይ በአማካኝ የሚኖራት የልጆች ብዛት፡፡

**Traditional birth attendant (TBA)**: የልምድ አዋላጅ

A traditional birth attendant is a person (usually a woman) who assists the mother during childbirth and who initially acquired her skills delivering babies herself or through apprenticeship to other traditional birth attendants. The TBA is generally an older woman who has borne one or more children herself and lives in the community in which she practices.
በራሳቸው በመማር ወይንም ሌሎች የልምድ አዋላጆች ሲያዋልዱ በማየት እናቶች በሚወልዱበት ወቅት የሚያግዙ ወይንም የሚያዋልዱ ሰዎች (በአመዛኙ ሴቶች) የልምድ አዋላጅ ይባላሉ፡፡ የልምድ አዋላጆች በአመዛኙ የልጆች እናቶች ሆነው በዛው በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

**Traditional Methods**: ባህላዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ

Include periodic abstinence also known as the calendar or rhythm method and withdrawal.
በቀን አቆጣጠር ዘዴ እርግዝና መከላከልንና የወንዱ ዘር(ስፐርም) ወደ ማኅጸን ከመግባቱ በፊት ብልትን በማውጣትና የወንድን ዘርን ከማኅፀን ውጪ የማፍሰስ ዘዴን ያካትታል፡፡

## Trained traditional birth attendant: የሰለጠነ/ች የልምድ አዋላጅ

A trained TBA is one who has undergone a short course of training conducted by the modern health care system to upgrade her skills.
የሰለጠነ/ች የልምድ አዋላጅ የሚባሉት በጤና ተቋማት አማካኝነት ሞያቸውን እንዲያሻሽሉ ስልጠና የተሰጣቸው አዋላጆች ናቸው፡፡

## Unmet need for family planning: ያልተሳካ የቤተሰብ ዕቅድ

The percentage of married, fecund women who prefer to space or limit their births but are not using contraception
ያገቡና በመውለጃ እድሜ ውስጥ ያሉ ሴቶች ሆነው አራርቀው ለመውለድ ወይም በዕቅድ ለመውለድ እየፈለጉ ነገር ግን የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን የማይጠቀሙ ሴቶች መጠን፡፡

## Unsafe abortion: ጥንቃቄ የጎደለው ጽንስ ማቋረጥ

Defined as a procedure for terminating an unwanted pregnancy either by persons lacking the necessary skills or in an environment lacking the minimal medical standards, or both. Unsafe abortions are characterized by the lack of inadequacy of skills of the provider, hazardous techniques, and unsanitary facilities.
አደገኛ ጽንስ ማቋረጥ ያልተፈለገ እርግዝናን እውቀቱ በሌላቸው ሰዎች አማካኝነት ወይንም ጽንስ ማቋረጡን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል ዘመናዊ ህክምና በሌለበት ሁኔታ ሲከናወን የሚፈጠር ነው፡፡ አደገኛ ጽንስ ማቋረጥ ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች መካከል የድርጊቱ ፈጻሚዎች በቂ የሆነ ክህሎት አለመኖር፣ አሰቃቂ የማቋረጥ ዘዴዎችን መጠቀምና ንጽህናውን ያልጠበቀ አካባቢ ይገኙበታል፡፡

## Vacuum aspiration፡ በመከስተኛ ቀዩ ጥገና ፅንስን ማቋረጥ

Usually performed on an outpatient basis, uses a tube inserted into the uterus to suction out the contents of the uterus; an electric pump or manual aspirator can be used in this procedure.
ይህ ዘዴ ወደ ማኅፀን በሚገባ ቱቦ መሰል መሳሪያ በማኅፀን ውስጥ ያለውን ነገር በመምጠጥ ፅንስን ያቋርጣል፡፡ በዚህ ዘዴ ህክምና ያገኙ ወዲያውኑ ወደቤታቸው መሄድ ይችላሉ፡፡

# 4 . የአካባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ሳይንስ ሞያዊ ሙዳይ ቃላት
**(Glossary of Environment and Environmental Health Terms)**

## 4.1. የአካባቢ ቃላት መፍቻ

**Adaptation**: ተላምዶ

Adjustment or preparation of natural or human systems to a new or changing environment which moderates harm or exploits beneficial opportunities.
ተፈጥሮ ወይም የሰው ልጅ ሊደርስበት የሚችልን አዲስ ወይም ተለዋዋጭ የአየር ንብረት ለውጥን ጉዳት ለመቀነስ ወይም በሁኔታው የተፈጠሩ ጠቃሚ እድሎችን ለመጠቀም ራስን ከሁኔታዎች ጋር ማስተካከል ወይም ማዘጋጀት መቻል ነው፡፡

**Adaptive capacity**: የተላምዶ አቅም

Adaptive capacity is defined as the ability of a system (human or natural) to adjust to climate change (including climate variability and extremes) to moderate potential damages, to take advantage of opportunities, or cope with the consequences. One of the most important factors shaping the adaptive capacity of individuals, households and communities is their access to and control over natural, human, social, physical and financial resources.
የተላምዶ አቅም ማለት የአየር ንብረት ለውጥ እና ተያያዥ ተፅዕኖዎችን በተመለከተ የተፈጥሮ ወይም የሰው ልጅ ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚፈጠሩ እድሎችን ለመጠቀም ወይም ተፅዕኖዎቹን ለመቋቋም የሚኖረው አቅም ማለት ነው፡፡ የግለሰቦችን፣ የቤተሰቦችን እና የማህበረሰቦችን የተላምዶ አቅም ከሚወስኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ለተፈጥሮ፣ ለሰው ኃይል፣ ለማህበራዊ፣ ለቁሳዊ እና ለገንዘባዊ ሀብቶች ያሏቸው ተደራሽነት እና የእነዚህን ሀብቶች ባለቤት የመሆን አቅም ነው፡፡

**Agriculture**: ግብርና

The active production of useful plants or animals in ecosystems that have been created by people. Agriculture may include cultivating the soil, growing and harvesting crops, and raising livestock. Steady improvements in tools and methods over the centuries increased agricultural output, as did mechanization, selective breeding and hybridization, and, beginning in the 20th century, the use of herbicides and insecticides.
በሰዎች የመኖሪያ አካባቢዎች ጠቃሚ የሆኑ አዝርዕትንና እንስሳትን የማልማትና የማርባት ተግባር እርሻ ይባላል፡፡እርሻ ከዚህም በተጨማሪ አፈርን መንከባከብን፣ የእህል አይነቶችን መዝራትና ማጨድን፣ ከብት ማርባትን ያጠቃልላል፡፡ በየዘመናቱ

የተፈጠሩት እንደ ሜካናይዝድ እርሻ፣ ምርጥ ዘር እና ማዳቀል እንዲሁም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ደግሞ የጸረ-ተባይና ጸረ-አረም መድሃኒቶችን የመሳሰሉ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችና የአስተራረስ ስልቶች የእርሻ ውጤቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ረድተዋል።

## **Biodiversity**፡ ብዘሀ ህይወት

Biodiversity means that there are many different types of species and that there is large-scale genetic variation within each of them.
ብዘሀ-ህይወት የተለያዩ ዓይነት ዝርያዎች ያሉ ሲሆን፤ በነዚህም መካከል ያሉ የተለያዩ የአፈጣጠር ልዩነቶች ማለት ነው።

## **Biodiversity conservation**: የብዝሃ ሕይወት አንክብካቤ

Conserve genetic resources and biological diversity more generally, enabling evolution to continue and providing raw materials for biotechnology.
ዝግመታዊ ለውጥ እንዲቀጥልና ለስነ-ህይወታዊ ቴክኖሎጂ ጥሬ እቃ ግብአትነት ጥቅም እንዲውሉ ለማስቻል ጭምር የዘረመል ሀብቶችና ሕይወታዊ ብዝሃነትን መንከባከብ

## **Biofuel**፡ አጸ - ነዳጅ

The joint name of fuels which originate from plants (biomass). This can include everything from wood and straw to refined biofuels such as pellets and ethanol. Biofuels are renewable because they can be re-created in a relatively short period of time once they have been used, as long as we do not consume more than we grow. Cutting down too many trees can have a negative effect on biodiversity. Peat is no longer regarded as a biofuel.
ምንጫቸው እጽዋት የሆኑ የሃይል ምንጮች ጥምር ስም እጸ-ነዳጅ ይባላል።ይህም ከእንጨት እና ከእህል ተረፈ ምርት የሚገኙትን ማናቸውንም የኃይል ምንጮች ሲያጠቃልል ፕሌትስና ኢታኖልም በዚሁ ምድብ ይገኛሉ።ባዮፊውሎች ታዳሽ ሀይል ናቸው። ምክንያቱም ካበቀልነው በላይ ካልተጠቀምን በስተቀር በንጽጽሮሽ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልሰን ልናዘጋጃቸው የምንችላቸው ናቸው። ዛፎችን መጨፍጨፍ በተለያዩ ፍጡራን ዝርያዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ያስከትላል። ከብስባሽ የሚገኝ የኃይል ምንጭ ከእጸ-ነዳጅ ክፍሎች ውስጥ አይመደብም።

## **Carbon sequestration**: ካርቦን መሰብሰብ / ማጠራቀም

Carbon sequestration is a method for managing the amount of carbon dioxide (C02) that is released into the atmosphere by burning carbon-based fuels—predominantly carbon-rich petroleum fuels. It is a relatively new idea brought about by the concern that high concentrations of atmospheric C02 contribute to global warming. In principle, carbon sequestration refers to storage of carbon that would otherwise be released into the atmosphere.

ካርቦን ማጠራቀም ማለት የካርቦንነት ይዘት ያላቸውን ነዳጆች በዋናነትም ካርቦን በብዛት የሚገኝባቸውን የቤንዚን ነዳጆች በማቃጠል ወደ ከባቢ አየር የተለቀቀውን የካርቦን ዳይኦክሳይድን መጠን የማመጣጠን ስልት ነው። ይህ ሃሳብ በንጽጽር ሲታይ ቅርብ ጊዜ የመጣ ሲሆን፤ በከባቢ አየር ውስጥ ከፍተኛ የካርቦን ዳይኦክሳይድ ክምችት መኖር ለዓለም የሙቀት መጠን መጨመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያመጣ ነው ከሚለው እሳቤ ጋር የተያያዘ ነው።

## Carbon cycle: የካርበን ዑደት

Carbon is continually exchanged between the atmosphere, ocean, biosphere, and land on a variety of ways. In the short term, CO2 is exchanged continuously among plants, trees, animals, and the air through respiration and photosynthesis, and between the ocean and the atmosphere through gas exchange. Other parts of the carbon cycle, such as weathering of rocks and the formation of fossil fuels, are much slower processes occurring over many centuries. For example, most of the world's oil reserves were formed when the remains of plants and animals were buried in sediment at the bottom of shallow seas hundreds of millions of years ago, and then exposed to heat and pressure over many millions of years. A small amount of this carbon is released naturally back into the atmosphere each year by volcanoes, completing the long-term carbon cycle. Human activities, especially the digging up and burning of coal, oil, and natural gas for energy, are disrupting the natural carbon cycle by releasing large amounts of "fossil" carbon over a relatively short time period.
ካርበን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በከባቢ አየር፣ በውቅያኖስ፣ በመሬት እና በዕፅዋት መካከል ይቀያየራል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ካርቦንዳይኦክሣይድ በዕፅዋት መካከል፣ በዛፎች፣ በእንስሳት እና በአየር መካከል የሚቀያየር ሲሆን በውቅያኖስና በከባቢ አየር መካከልም በጋዝ ልውውጥ መልክ ይቀያየራል።ከአለት፣ በአየር ጠባይ መለዋወጥ እና ከነዳጅ መፈጠር ጋር በተያያዘ የሚኖረው የካርበን ዑደት እጅግ ዘገምተኛ በመሆኑ ብዙ ክፍለ-ዘመናትን የሚወስድ ሂደት ነው። ለምሳሌ ያህል አብዛኛው የዓለማችን የነዳጅ ክምችት የተፈጠረው ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የዕፅዋትና የእንስሳት ቅሪቶች ከውቅያኖስ በታች በአሸዋ ሥር በተቀበሩ ጊዜ ነው። ከዚህ ካርበን ውስጥ ጥቂት ብቻ በየዓመቱ የካርበን ዑደት በማጠናቀቅ በእሣተ ገሞራ አማካኝነት ወደ ከባቢ አየር ይለቀቃል። እንደ ከሰል፣ ነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ የማውጣትና በማቃጠል ተግባራት ላይ ያሉ ሰዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ካርበን እንዲለቀቅ በማድረግ የተፈጥሮው የካርበን ዑደት እንዲዛባ ያደርጋሉ።

## Climate change Mitigation: የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል

Climate Change Mitigation refers to efforts to reduce or prevent emission of greenhouse gases. Mitigation can mean using new technologies and renewable energies, making older equipment more energy efficient, or changing management practices or consumer behavior. It can be as complex as a plan for a new city or as a simple as improvements to a cook stove design.
የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል አካባቢን የሚጎዱ ጋሶችን ልቀት የመቀነስ ወይም

የመከላከል ተግባርን ያመላክታል። የመከላከል ወይም የማሻሻል ሥራው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ወይንም ታዳሽ ሃይሎችን መጠቀምን፣ የአሮጌ መሳሪያዎችን የኢነርጂ አጠቃቀምን ውጤታማ ማድረግን ወይም የአጠቃቀም ስልታችንን የተሻለ የማድረግ ሂደትን ያጠቃልላል። የአየር ንብረት ለውጡን የመከላከልና የመታደጉ ሥራ አዲስ ከተማን የመገንባትን ያህል ውስብስብ ወይንም የማብሰያ ምድጃን ዲዛይን የማሻሻልን ያህል ቀላል ሊሆን ይችላል።

## Compost: ቀልዝ

Compost is the process which occurs when plant and food waste, in conditions in which oxygen is available, is broken down to produce soil (humus). Humus can be used in parks, gardens and agriculture.
ኦክስጅን በሚገኝበት ቦታ ላይ እጽዋትንና ተረፈ-ምግብን ሰባብሮ በማከማቸት ለመሬት ማዳበሪያነት ወይም ፋልማ መሬትን የማዘጋጀት ሂደት ነው። ቀልዝ ለመናፈሻዎች፣ ለጓሮ ተክል እና ለእርሻ ሥራ ይውላል።

## Cultural values: ባህላዊ እሴቶች

culturally important sites and resources,
ባህላዊ ጠቀሜታ ያላቸው አካባቢዎችና ሀብቶች ።

## Disaster: ውድመት

Disaster is a serious disruption of the functioning of a community or a society causing widespread human, material, economic or environmental losses which exceed the ability of the affected community or society to cope using its own resources. A disaster is a function of the risk process. It results from the combination of hazards, conditions of vulnerability and insufficient capacity or measures to reduce the potential negative consequences of risk.
መጠነ-ሰፊ የሆነ በሰው፣ በቁሳቁስ፣ በኢኮኖሚ ወይም በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳት ሲሆን ይህም ተጐጂው ማህበረሰብ ወይም ህብረተሰብ ያሉትን ሀብቶች በመጠቀም ለመቋቋም ከሚችልበት ደረጃ የበለጠ የከፋ ነው። ውድመት የስጋት ሂደቶች ድምር ውጤት ሆኖ የአደጋ ክስተቶች ተጋላጭ የመሆን ሁኔታዎች፣ ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የአቅም አለመኖር በጋራ የሚያስከትሉት ሁኔታ ነው።

## Disaster risk management (DRM): የአደጋ ሥጋት ቁጥጥር

It is the systematic approach to avoiding, transferring, and reducing the adverse impacts of hazard events. It includes a range of activities that are frequently presented as a cycle including prevention/mitigation, preparedness, response, and recovery.
የአደጋ ሥጋት ቁጥጥር ማለት የአደጋ ክስተቶችንና ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለማሻለፍ እና ለመቀነስ የሚደረግ ስርአት የያዘ የአተገባበር ሂደትን ያመለክታል፡ ፡ በዚህ የቁጥጥር ሂደት ውስጥም ብዙ ጊዜ እንደ አንድ ዑደት የሚታዩ ተግባራት

የሚካተቱበት ሲሆን እነዚህም መከላከል/መቀነስ፣ ዝግጁነት፣ ምላሽ መስጠት እና ማገገም ናቸው፡፡

**DDT**: ዲዲቲ

DDT is a highly environmentally-hazardous and toxic insecticide which is banned in many countries.
ዲዲቲ በከፍተኛ ሁኔታ አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትል መርዛማ የጸረ-ተባይ መድሃኒት ሲሆን፤ በዚህም የተነሳ ብዙ አገሮች በጥቅም ላይ እንዳይውል አግደውታል፡፡

**Ecology**፡ ስነ-ምህዳር

The study of the interplay between living organisms and their surroundings
ስነ-ምህዳር በህይወት ባሉ ፍጡራንና በአካባቢያቸው መካከል ስላለው ትስስር የሚያጠና የሳይንስ መስክ ነው፡፡

**Eco management systems**፡ የአካባቢ አመራር ሥርዓት

Are being used by more and more companies as a tool to obtain a better overview of the environmental impact their operations have. An effective eco management system can also help a company to control and limit this environmental impact.
የአካባቢ አመራር ሥርዓት በርካታ ድርጅቶች ያላቸው ምርትና አሰራር በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ አስመልክቶ የሚከታተሉበት መንገድ ነው፡፡ ውጤታማ የሆነ የአካባቢ አመራር ሥርዓትን ማስፈን ድርጅቱ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ጫና ለመቀነስም ሆነ ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡

**Energy**፡ ኃይል

Energy cannot be destroyed only converted. Energy sources can be divided into three main groups — solar energy, fossil fuels and nuclear energy. Energy can be used for work, lighting, heating and transport. In principle, all energy use has an environmental impact, but the impact varies depending on the source of energy that is used.
ኃይልን ወደ ሌላ ነገር መቀየር እንጂ ማውደም አይቻልም፡፡ የኃይል ምንጮች በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም የጸሐይ ኃይል፣ የፎሲል ኃይል እና የኒኩለር ኃይል ናቸው፡፡ የኃይል ምንጮች ለሥራ፣ ብርሃን ለማግኘት፣ ለሙቀትና ለመጓጓዣ አገልግሎት ይውላሉ፡፡ በመሠረቱ ሁሉም የኃይል ምንጮች በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ አለ፡፡ ይሁን እንጂ የጥፋቱ መጠን በምንጠቀመው የኃይል ምንጭ አይነት ይለያያል፡፡

**Environmental audit**፡ የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት

A systematic evaluation to ensure that a company's eco management system is working and those environmental programmes are being run according to the law and in a satisfactory manner by internal standards. During this audit, the company's effect on the external environment,

the way the internal organization handles environmental issues and the documentation which is designed to guide and control environmental programs are all examined.
የአካባቢ ኦዲት አንድ ድርጅት የሚጠቀመው የአካባቢ አመራር ሥርዓት በትክክል መተግበሩን የመከታተያ መንገድ ሲሆን፤ የአካባቢ መርሃ ግብሮችም በአለም አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን መከታተያ ሥርዓት ነው። የኢዲት ክትትሉ በሚደረግበት ወቅት ድርጅቱ ከይዞታው ውጪ ባለው አካባቢ ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ፣ ድርጅቱ የአካባቢ ጉዳዮችን የሚከታተልበት እና የሚያከናውንበት መንገድ፤ እንዲሁም የአካባቢ መርሃ ግብሮችን ለመምራት ታስበው የተዘጋጁ ሰነዶች በሙሉ ይታያሉ።

## Environmental economy: የአካባቢ ምጣኔ ኃብት

The part of national economy which attempts to integrate an economic approach with an ecological one. In short, it would be true to say that environmental economy constitutes an attempt to make concealed environmental costs visible
የምጣኔ ኃብት አሠራርን ከአካባቢ ጉዳይ ጋር ለማስተሳሰር የሚደረግ የአገራዊ ምጣኔ ኃብት አንዱ ክፍል ነው። በአጭሩ የአካባቢ ምጣኔ ኃብት ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በግልጽ እንዲታዩ ማስደረጊያ መንገድ ነው።

## Ethanol፡ ኢታኖል

The name given to alcohol which can be used as a renewable fuel in vehicles
ኢታኖል ለተሽከርካሪዎች የሚውል ታዳሽ የሆነ ለአልኮል ነዳጅ የተሰጠ ስያሜ ነው።

## Fossil fuels፡ የተፈጥሮ ነዳጅ

Fossil fuels consist of plants and parts of plants which sank into the earth's crust millions of years ago and were transformed into fossil material (coal, gas and oil). Fossil fuels are an example of stored resources. When fossil fuels are burnt, carbon dioxide is produced, among other things. As this carbon is not a natural part of the biological cycle, the atmosphere receives additional carbon dioxide which helps to produce global warming.
ተፈጥሮ ነዳጅ ከሚልዮን አመታት በፊት ወደ መሬት የውስጠኛው አካል ሰርገው ወደ ነዳጅ ኃይልነት ከተቀየሩ እጽዋት እና የእጽዋት ክፍሎች የሚገኝ ሲሆን ይህም ከሰልን፣ ጋዝንና ነዳጅን ያጠቃልላል። ይህ የኃይል ምንጭ የተከማቸ ኃብት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ሃይል ሲቀጣጠል ከሚፈጠሩት ነገሮች መካከል ካርቦን ዳይኦክሳይድ አንዱ ነው። ይህ ካርቦን ደግሞ የተፈጥሮ የአየር ዝውውሮሹ አካል ባለመሆኑ ከባቢው አየር ተጨማሪ ካርቦን ዳይኦክሳይድ እንዲወስድ በማድረግ ለአለም የሙቀት መጠን መጨመር አስተዋጽኦ ያበረክታል።

## Greenhouse Gas (GHG) Effect: የግሪንሀውስ ጋዝ ተፅእኖ

The greenhouse effect is a natural phenomenon that is essential for

keeping the Earth's surface warm. Like a greenhouse window, greenhouse gases allow sunlight to enter and then prevent heat from leaving the atmosphere. These gases include carbon dioxide (CO2), methane (CH4), nitrous oxide (N2O), and water vapor. Human activities, especially burning fossil fuels, are increasing the concentrations of many of these gases, amplifying the natural greenhouse effect.
የግሪንሀውስ ጋዝ ተፅእኖ  የምድር ገፅ (ዓለማችን)ሙቀት እንዲኖረው የሚያደርግ ተፈጥሮአዊ  ክስተት ነው፡፡ ልክ እንደ ግሪንሀውስ  መስኮት የግሪንሀውስ ጋዞችም የፀሐይ ብርሃን ወደ ከባቢ አየር እንዲገባና ሙቀት ከከባቢ አየር እንዳይወጣ ከሚፈለገው በላይ የሆነ የፀሐይ ሙቀት እንዲቀር ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ጋዞችም ካርቦን ዳይኦክሳይድ(CO2)፣ ሚቴን(CH4)፣ ኒትረስ ኦክሣይድ(N2O) እና የውሃ ትነት ናቸው፡፡ እንደ የነዳጅ ማቀጣጠል ያሉ የሰዎች ተግባራት የብዙ ግሪንሀውስ ጋዞች ክምችት እንዲባባስ ያደርጋሉ፡፡

## Hazard: አደጋ

In the context of disaster risk reduction, hazard is defined as a potentially dangerous phenomenon or human activity that may cause the loss of life or injury, property damage, loss of livelihoods, social and economic disruption or environmental degradation. Natural hazards can be classified according to their geological (earthquake, tsunamis, volcanic activity), hydrometeorological (floods, tropical storms, drought) or biological (epidemic diseases) origin.
አደጋ ማለት ሁኔታዎችን ሊያቃውስ የሚችል አደገኛ ክስተት ወይም በሰዎች ድርጊት ምክንያት የሚደርስ የህይወት መጥፋት ወይም የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት፣ የኑሮ መናጋት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ  ወይም አካባቢያዊ ሁኔታዎች መቃወስን የሚያስከትል ተግባር  ነው፡፡ የተፈጥሮ አደጋዎች በጂኦሎጂካል (የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የሱናሚ ክስተቶች፣ የእሳተ-ገሞራ ክስተቶች) ወይም በባዮሎጂካል (የበሽታ ወረርሽኝ) ወይም በሃይድሮ-ሜትዎሮሎጂካል (የጐርፍ መጥለቅለቅ፣ አውሎ ነፋስ፣ ድርቅ ወ.ዘ.ተ) መንስኤዎቻቸው መሰረት ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡

## Hydropower፡ የውሃ ኃይል

Is generated indirectly by the sun when water is heated, falls as rain and fills watercourses. In principle, hydropower produces no emissions, but it still has a major impact locally and regionally and changes the living conditions in and around the watercourses where dams are built. Flows are changed by dams, and rivers in some areas are drained. Dams flood areas so that the plants and animals that previously lived there disappear and the people who live there are forced to move.
የውሃ ኃይል የሚመነጨው በተዘዋዋሪ መንገድ በጸሃይ አማካኝነት ውሃ ሲሞቅ፣ በዝናብ መልክ  እና በፏፏቴ መልክ ሲወርድ ነው፡፡ በመሰረቱ የውሃ ኃይል የሚበክል ልቀት የለውም፡፡ ነገር ግን ግድቦች በሚገነቡ ጊዜ በውሃው ውስጥና በውሃው አካባቢ ባሉ የአኗኗር ሁኔታዎች ላይ የሚያስከትለው ጉልህ አካባቢያዊና ክልላዊ ተጽእኖ አለው፡፡ ለምሳሌ የወንዞች መደበኛ ጉዞ እንዲቀለበስ ሲያደርግ እንደውም በአንዳንድ አካባቢዎች የወንዞች ድርቀትን ያስከትላል፡፡ ግድቦች አካባቢዎችን ስለሚያጥለቀልቁ

ቀድሞ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩትን እንስሳትና እጽዋት እንዲጠፉ የሚያደርጉ ሲሆን፤ የአካባቢውን ነዋሪዎችም ያፈናቅላል፡፡

## Maintain soil fertility: የአፈር ለምነትን መጠበቅ

Build soils, control soil erosion, and recycle nutrients.
በየጊዜው የአፈር ለምነትን በማሻሻል፣የአፈር መሸርሸርን በመቆጣጠርና በአፈር ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ንጥረነገሮች ተመልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማደረግ አፈር ለምነቱን እንዳያጣ የማድረግ ስራ ነው፡፡

## Microclimate stabilization: የአንድ አካባቢን የአየር ንብረት ማረጋጋት

Ameliorate local climate conditions and provide amenity values to nearby communities
የአንድ አካባቢን የአየር ንብረትን በማረጋጋት እና በማሻሻል በአቅራቢያው የሚገኘው ማህበረሰብ የተመቻቸ እና አስደሳች የሆነ አካባቢ እንዲያገኝ ማድረግ፡፡

## Natural gas: የተፈጥሮ ጋዝ

A fossil fuel which is stored in the earth's crust. Causes fewer emissions of carbon dioxide and sulphur than oil incineration. In some cases, natural gas can be replaced by biogas, which is a renewable fuel.
ይህ ኃይል በመሬት የውስጠኛው አካል ተከማችቶ የሚገኝ የተፈጥሮ ኃይል ምንጭ ነው፡፡ ዘይትን በማቃጠል ከሚገኘው ኃይል በተሻለ መጠነኛ የሆነ የካርቦን ዳይኦክሳይድ እና ሰልፈር ልቀትን ያስከትላል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጥሮ ጋዝ ታዳሽ ነዳጅ በሆነው ባዮጋዝ የሚተካበት ጊዜ አለ፡፡

## Nuclear energy: የኒውክሌር ኃይል

Nuclear energy is a relatively new energy form which utilizes the energy which holds two atoms together. Splitting them produces energy which we call nuclear power. The radioactive substance uranium is used for this purpose and, when it is split, it produces other radioactive fission products. The principal environmental problems when it comes to nuclear energy are the handling and emission of radioactive substances. Because of the disastrous effect these substances have on living organisms such as cancer and genetic defects, nuclear power is strictly regulated in most countries.
የኒውክሌር ኃይል በንጽጽሮሽ ሲታይ በቅርብ ጊዜ የተገኘ የኃይል ምንጭ ሲሆን በውስጡም ሁለት አቶሞችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ የራዲዮ አክቲቭ አካል የሆነው ዩራኒየም ለዚህ አገልግሎት የሚውል ሲሆን፤ ይህም እንዲለያይ በሚደረግበት ጊዜ ሌላ የሬዲዮ አክቲቭ ሃይል አመንጪ ምርት ይሰጣል፡፡ የዚህ ኃይል ከአካባቢ ጋር ያለው ችግር ከአያያዝና አጠባበቁ እንዲሁም ከሬዲዮ አክቲቭ ልቀቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ኃይል ውስጥ ያሉት ንጥረ ነገሮች ካንሰርንና የአፈጣጠር ችግሮችን ስለሚያስከትሉ በርካታ አገሮች የኒውክሌር ኃይል ማመንጨትን በህግ ከልክለዋል፡፡

## Ozone layer (O3): የኦዞን ንጣፍ

A thin layer of ozone which provides protection from the sun's harmful UV radiation. The current increase in the occurrence of skin cancer is thought to be due in part to the depletion of the ozone layer. In recent years, it has been depleted and has temporarily disappeared in certain areas — primarily around the Poles.
የኦዞን ንጣፍ ከጸሀይ የሚለቀቀውን አደገኛ የሆነ ዩቪ የተሰኘ ጨረር የሚከላከል ስስ የሆነ አካል ነው። በቅርቡ እየተከሰተ ያለው የቆዳ ካንሰር ከዚሁ ከኦዞን ድርብርብ መሳሳት ጋር በተያያዘ የተከሰተ ነው ተብሎ ተገምቷል። በቅርብ አመታት በተለይም በምድር ዋልታዎች አካባቢ ከፍተኛ መሳሳትና በአንዳንድ አካባቢዎችም ከነጭራሹ የመጥፋት ሁኔታ ታይቶበታል።

**Provide forest products**: **የደን ውጤቶችን ማቅረብ**

Provide a wide range of non-timber forest products, in addition to various timber products.
የተለያዩ የደን ውጤቶችን ማለትም የጣውላ ምርትን ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ የደን ውጤቶችን ማቅረብ።

**Renewable energy**: **ታዳሽ ኃይል**

Renewable types of energy include solar power, wind power and hydropower and different types of biofuel. The basic feature of renewable energy is that it can be re-created within a foreseeable period, with the exception of the sun which constantly generates energy.
ታዳሽ ኃይል ከሚባሉት መካከል የጸሃይ ኃይል፣ የንፋስ ኃይል፣ የውሃ ኃይል እና የተለያዩ አይነት የባዮፊውል አይነቶች ይገኙበታል። የዚህ የታዳሽ ሃይል ልዩ ባህሪ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንደገና ተመልሶ ሊፈጠር መቻሉ ሲሆን፣ በቋሚነት ኃይል ከምታመነጨው ከጸሀይ ኃይል ግን በፍጹም የተለየ ነው።

**Renewable water**: **ሊጣራ የሚችል ውሃ**

The surface water runoff from local precipitation, the inflow from other regions, and the ground water recharge that replenishes aquifers
ከአካባቢ ዝናብ የሚገኝ የመሬት ላይ ውሃ፣ ከሌላ አካባቢ ሰርጎ የሚገኝ ውሃ እና የከርሰ ምድር ውሃ ተጣርተው በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

**Research and education importance**: **ለምርምርና ትምህርት ምቹ ሁኔታ መኖር**

Provide sites for scientific research and education on a wide range of ecological, social, and economic issues.
ስፋት ባላቸው የስነምህዳር፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ ምርምር ለማካሄድና ትምህርት ለመስጠት የሚሆኑ ቦታዎችን ማመቻቸት

**Resilience**: **ዱንገተኛ አደጋን የመቋቋም ብቃት**

Resilience can be defined as the ability of a system (human or natural) to resist, absorb, and recover from the effects of hazards in a timely and efficient manner, preserving or restoring its essential basic structures, functions and identity. Resilience is a familiar concept in the context of disaster risk reduction (DRR), and is increasingly being discussed in the field of adaptation. A resilient community is well-placed to manage hazards, to minimize their effects and/or to recover quickly from any negative impacts, ድንገተኛ አደጋን የመቋቋም ብቃት የሰው ልጅ ወይም ተፈጥሮ ለድንገተኛ አደጋዎች ያለው የመከላከል፤ የመቋቋም እና የማገገም ሥርአት ያለው ብቃት ሲሆን፤ ይህም ወቅቱን በጠበቀና ውጤታማ በሆነ መልኩ፣ የበፊቱን መሰረታዊ ቅርጽ፣ አሠራርና ማንነት ጠብቆ በማቆየት ደረጃ የሚከናወን ነው። ይህ ሃሳብ ከድንገተኛ አደጋዎች ቅነሳ ሃሳብ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሲሆን፤ በተለይም በመላመድ ዘርፍ ውስጥ ተደጋግሞ የሚነሳ ነው። ድንገተኛ አደጋን የመቋቋም ብቃት ያለው ማህበረሰብ አደጋዎችን በሚቋቋምበት ደረጃ፣ ክስተታቸውን ዝቅተኛ በሚያደርግበትና ከአደጋቸውም ፈጥኖ በሚያገግምበት ደረጃ የተደራጀ ነው።

## Risk: ስጋት

Risk is the probability of harmful consequences, or expected losses (deaths, injuries, property, livelihoods, economic activity disrupted or environment damaged) resulting from interactions between natural or human-induced hazards and vulnerable conditions.
ስጋት ማለት በተፈጥሯዊ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋዎች እና የተጋላጭነት ሁኔታዎች መካከል ካለው ተያያዥነት የተነሳ ጉዳ የሆኑ ክስተቶች ወይም አደጋዎች (የህይወት መጥፋት፣ ጉዳት፣የኑሮ መናጋት፣ የንብረት ውድመት፣ የኢኮኖሚ መናጋት፣ የአካባቢ መጐዳት) የመከሰት እድልን የሚያመለክት ነው።

## Salinization: የመሬት ጨዋማነት

The buildup of salts in soils Occurs frequently from over irrigated soil when evaporation of water at the surface draws salts from underground rocks and soils, causing salts to crystallize and interfere with root growth.
በመሬት ላይ የጨው መጠን መጨመር ሲሆን፤ በአመዛኙም የሚታየው የበዛ የመስኖ ውሃ ፍሰት በሚያጋጥማቸው መሬቶች ላይ ሲሆን የሚፈጠረውም መሬት ውስጥ በሚገኙ አለቶች አማካኝነት በሚከሰት የውሃ ትነት ነው።

## Storm protection: ከባድ ማእበልን መከላከል

Protect coastlines against damage from storms (especially coral reefs and mangroves), and absorb heavy rainfall (especially wetlands and forests).
የባሕር ዳርቻዎች በከባድ ማእበል (በተለይ የባህር ወለል ንጣፎችና የበረሃ ዛፎች)እና በከፍተኛ ዝናብ(በተለይ ረግረጋማ ስፍራዎችና ደኖች) እንዳይጐዱ መከላከል።

## Tourism: ቱሪዝም

Making a holiday involving an overnight stay away from the normal place

of residence. This is in contrast to recreation which involves leisure activities lasting less than twenty-four hours. This holiday may be based on the cultural, historic, and social attractions of an urban centre, or on the appeal of a different environment.
ቱሪዝም መደበኛ አካባቢን ለቆ ወደ ሌላ ስፍራ በመሄድ የሚከናወን የእረፍት ጊዜን የማሳለፊያ ተግባር ነው፡፡ ቱሪዝም ከ24 ሰዓት በታች ከሚወሰደውና ለመዝናናት ከሚከናወነው ተግባር የተለየ ነው፡፡ ይህ የእረፍት ጊዜን የማሳለፍ ተግባር በከተማ አካባቢ ወይም በሌሎች ስፍራዎች ያሉ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ቦታዎች የመጎብኘትን ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡

## The CRGE strategy: የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ

The Ethiopia's Climate Resilient Green Economy (CRGE) Strategy prepared in 2011 by the Government of Ethiopia has the strategic vision to enable the country achieve a middle-income status by the year 2025 through a climateresilient green Economy; achieve country development goals(GTP targets) and MDGs in a sustainable way; a transition to low carbon and energy efficient economy; and enable to follow a green growth path that fosters economic development and environmental sustainability towards creating a green economy
የኢትዮጵያ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በሀገሪቱ መንግሥት በ2003ዓ.ም (2011 እ.ኤ.አ) የተዘጋጀ ሲሆን እንደ ራዕይ የያዘውም ሀገሪቱ በ2017 ዓ.ም (2025 እ.ኤ.አ) መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ጐራ ለመቀላቀል ትችል ዘንድ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚ የልማት ስትራቴጂን መተግበር ነው፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድንና የምዕተ-ዓመቱን ግቦች ማሣካት፣ ከካርበን ልቀት የነጻ እና ኃይል ቆጣቢ ወደሆነ ኢኮኖሚ መሸጋገር፣ በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ የማያስከትል ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና የአካባቢ ዘላቂነትን ማረጋገጥ የስትራቴጂው ዓላማዎች ናቸው፡፡

## Watershed protection: የተፋሰስ ጥበቃ

Protect watersheds for downstream hydroelectric, irrigation, and water supply installations.
የውሃ ተፋሰሶችን በታችኛው የውሃው ተፋሰስ አካባቢ ለሚከናወኑ ሃይል ማመንጫዎች፣ የመስኖ ሥራ፣ እና ለውሃ አቅርቦት ሥራዎች ሊውሉ በሚችሉበት መልኩ መንከባከብ፡፡

## Wind power፡ የንፋስ ኃይል

Indirect energy from the sun which is produced when air is heated and rises upwards and is replaced by cooler air from the side, thereby creating circulation. Wind power has very little environmental impact.
የሞቀ አየር ወደላይ በመነሳ ተመልሶ ከጎኑ ባለ ቀዝቃዛ አየር እንዲተካ አድርጎ የአየር ዝውውርን በመፍጠር በተዘዋዋሪ መንገድ ከሚፈጠር የጸሃይ ኃይል የሚገኘው ኃይል የንፋስ ኃይል ይባላል፡፡ የንፋስ ኃይል በአካባቢ ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ በጣም አነስተኛ ነው፡፡

## 4.2. የአካባቢ ሳይንስ ቃላት መፍቻ

**Absorption፡ መሰረግ**

The process of taking in, as when a sponge takes up water. Chemicals can be absorbed into the bloodstream after breathing or swallowing. Chemicals can also be absorbed through the skin into the bloodstream and then transported to other organs.
ልክ ስፖንጅ ውሃ እንደሚመጠው አይነት አንድን ነገር ወደ ውስጥ የማስገባት ሂደት ነው፡፡ በምንተነፍስበት ወይንም በምንውጥበት ወቅት ኬሚካሎች ወደ ደም ስሮቻችን ሰርገው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ኬሚካሎች በተመሳሳይ ሁኔታ በቆዳ አማካኝነት ሰርገው በመግባት ወደ ደም ስር ከገቡ በኋላ ወደ ዋና ዋና የሰውነታችን አካላት ሊዘልቁ ይችላሉ፡፡

**Ambient፡ የውጭ አየር**

Ambient air usually means outdoor air (as opposed to indoor air).
የውጭ አየር ማለት ከቤት ውጪ የሚገኝ አየር ነው (ከቤት ውስጥ አየር በተቃራኒ)፡፡

**Bedrock፡ ንጣፍ አለት**

The solid rock underneath surface soils
ከወለል አፈር በታች የሚገን ንጣፍ አለት፡፡

**Biological monitoring፡ ስነ-ህይወታዊ ትንተና**

Analyzing chemicals, hormone levels or other substances in biological materials (blood, urine, breath, etc.) as a measure of chemical exposure, health status, etc. in humans or animals.
በህዋሳዊ አካሎች (ደም፣ ሽንት፣ ትንፋሽ…) ላይ የሚገኙ ኬሚካሎችን፣ የሆርሞን ብዛቶችን እና ሌሎች አካላትን የመተንተን ዘዴ ስነ-ህይወታዊ ትንተና ይባላል፡፡ ትንተናው የሰውንና የእንስሳትን ለኬሚካል የመጋለጥ ደረጃን ለመለካትና የጤንነት ሁኔታን ለማወቅ የመሠራ ነው፡፡

**Body burden፡ አካላዊ ጫና**

The total amount of a chemical in the body. Some chemicals build up in the body because they are stored in body organs like fat or bone or are eliminated very slowly.
በሰውነት ውስጥ የሚገኝ አጠቃላይ የኬሚካል መጠን ማለት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ኬሚካልሎች በሰውነት ውስጥ የተገነቡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የሚከማቹት በሰውነታችን አካላት ውስጥ ባሉ እንደ ስብ እና አጥንት ያሉ አካላት ውስጥ ሲሆን በአዝጋሚነት የሚወገዱ ናቸው፡፡

**Case control study**፡ ንጽጽራዊ ጥናት

A study in which people with a disease (cases) are compared to people without the disease (controls) to see if their past exposures to chemicals or other risk factors were different.
ይህ ጥናት በበሽታ የተጠቁ ሰዎችን ካልተጠቁ ሰዎች በማነጻጸር ቀድሞ ለኬሚካሎች ወይም ለሌሎች ጠንቆች የመጋለጥ ደረጃቸውን የማጥኛ መንገድ ነው፡፡

**Central nervous system (CNS)**፡ ማዕከላዊ የነርቬ ሥርዓት

The part of the nervous system that includes the brain and the spinal cord.
የነርብ ሥርዓት አካል ሲሆን ይህም አንጎልንና ህብለ-ሰረሰርን የሚያጠቃልል ነው፡፡

**Climate change**፡ የአየር ንብረት ለውጥ

Refers to any change in climate over time, whether due to natural variability or as a result of human activity.
የአየር ንብረት ለውጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተፈጥሮ ክስተት ወይም በሰው ልጅ አማካኝነት የሚከሰት የአየር ንብረት ለውጥ ነው፡፡

**Cohort study**፡ በቡድን ክፋፍሎ ማጥናት

A study in which a group of people with a past exposure to chemicals or other risk factors are followed over time and their disease experience compared to that of a group of people without the exposure.
ይህ ጥናት የተወሰኑ ሰዎችን በቡድን በማድረግ ለኬሚካል ወይም ለሌላ ጠንቅ ያላቸውን የተጋላጭነት ታሪክ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በመከታተል ከሌሎች ካልተጋለጡ ሰዎች ቡድን ጋር በማነጻጸር የማጥናት ስልት ነው፡፡

**Contaminant**፡ በካይ

Any substance that enters a system (the environment, human body, food, etc.) where it is not normally found. Contaminants are usually referred to in a "negative" sense and include substances that spoil food, pollute the environment or cause other adverse effects.
ማንኛም ቁስ በፊት የማይኖርበት ወይም የማይገኝበት ሥርዓት (በአካባቢ፣ በሰው ልጅ አካል ፣ በምግብ) ውስጥ ገብቶ ሲገኝ በካይ ይባላል፡፡ በካይ ብዙውን ጊዜ በአሉታዊ ጎኑ ከብክለት ጋር በተያያዘ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህም የተመረዘ ምግብ፣ የተበከለ አካባቢ ወይም ለሌላ አደገኛ ነገር ውጤት እንጠቀምበታለን፡፡

**Dose**፡ መጠን

The amount of substance to which a person is exposed
ለሰው ልጅ የተሰጠ የአንድ ንጥረ ነገር መጠን፡፡

**Epidemiology**፡ የወረርሽኝ/የድንገተኛ ጤና አደጋ ጥናት መስክ

The study of the occurrence and causes of health effects in human populations. The investigators try to determine if the factor is associated with the health effect.
በሰው ልጅ ጤና ላይ የሚከሰቱ የጤና ጠንቆችን መከሰትና የመከሰቻ ምክንያታቸውን የሚያጠና ዘርፍ ነው። ጥናቱን የሚያካሂዱት ሰዎች በጥናት ሂደታቸው የተከሰተው አደጋ ለጤና ጠንቅ መሆን አለመሆኑን ይወስናሉ።

**Exposure**፡ ተጋላጭነት

Contact with a chemical by swallowing, by breathing or by direct contact (such as through the skin or eyes). Exposure may be either short term (acute) or long term (chronic).
የአንድ ሰው በመዋጥ፣ በመተንፈስ ወይንም ቀጥታ በመነካካት (ለምሳሌ በቆዳ ወይንም በአይን) ከኬሚካል ጋር ያለው የንክኪ መጠን ነው። ተጋላጭነቱ አጣዳፊ ወይንም የረጅም ጊዜ ሊሆን ይችላል።

**Exposure assessment**፡ የተጋላጭነት ዳሰሳ

A process that estimates the amount of a chemical that enters or comes into contact with people or animals. An exposure assessment also describes how often and for how long an exposure occurred, and the nature and size of a population exposed to a chemical.
ወደ ሰው ወይንም ወደ እንስሳት የገባውን የኬሚካል መጠን የመገመቻ ሂደት ነው። ዳሰሳው በየስንት ጊዜ እና ለምን ያህል ጊዜ እርዝመት ተጋላጭነቱ እንደተከሰተ እንዲሁም በተጋለጠው ወገን ተፈጥሮ እና መጠን ላይ ትንተና ይሰጣል።

**Feasibility Study (FS)**፡ የአዋጭነት ጥናት

A study that compares different ways to clean up a contaminated site. The feasibility study recommends one or more actions to remediate the site.
በዚህ ዘርፍ የብክላ ማስወገጃ መንገዶች ጥናት የሚካሄደው አንድን የተበከለ አካባቢ ከብክላ ለማጽዳት ያሉትን የተለያዩ መንገዶች በአማራጭነት በማመዛዘን ነው። የአዋጭነት ጥናቱ አካባቢውን ከብክለት ለማጽዳት አንድ ወይም በርካት እርምጃዎችን ሊያመላክት ይችላል።

**Health registry**፡ የጤና ምዝገባ

A record of people exposed to a specific substance (such as a heavy metal), or having a specific health condition (such as cancer or a communicable disease).
የጤና ምዝገባ የሰዎችን ለአንድ ንጥረ ነገር (ለምሳሌ ለከባድ የኬሚካል መጠን ወይንም ብረት) ወይም ለተለየ የጤና ሁኔታ (ለምሳሌ ለካንሰር ወይንም ለተላላፊ በሽታ) ያላቸውን ተጋላጭነት መዝግቦ የመያዣ ዘዴ ነው።

**Ingestion**፡ በአፍ መውሰድ

Swallowing (such as eating or drinking). Chemicals in or on food, drink, utensils, cigarettes, hands, etc. can be ingested. After ingestion, chemicals may be absorbed into the blood and distributed throughout the body.
በመመገብ ወይም በመጠጣት አንድን ነገር በአፍ መውሰድ መዋጥ ይባላል፡፡በምግብ፣ በመጠጥ፣ በምግብ ቤት እቃዎች፣ በሲጋራ ወይም በእጃችን ላይ ወይንም ውስጥ ያሉ ኬሚካሎችን ልንውጥና ወደ ሰውነታችን ልናስገባ እንችላለን፡፡ ከመዋጥ በኋላ ኬሚካሎች ወደ ደም ሥራችን ሊሰርጉና በዚያም አድርገው ወደ ሰውነታችን ክፍሎች ሊሰራጪ ይችላሉ፡፡

**Inhalation**: አየር መማግ

People can take in chemicals by breathing contaminated air.
ሰዎች የተበከለ አየር በሚምጉበት ወቅት ኬሚካል ወደ ውስጣቸው ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡

**Latency period**: ከተጋላጭነት እስከ ህመም ደረጃ ያለ ክፍለ-ጊዜ

The period of time between exposure to something that causes a disease and the onset of the health effect. Cancer caused by chemical exposure may have a latency period of 5 to 40 years.
ሰዎች ለአንድ ንጥረ ነገር ከተጋለጡበት እስከ በዚያው ምክንያት ለበሽታ እስከ ተጋለጡበት ጊዜ ድረስ ያለው ክፍለ-ጊዜ ነው፡፡ ለኬሚካል በመጋለጥ ሳቢያ የሚከሰት የካንሰር ህመም ከተጋላጭነት እስከ ህመምተኝነት ያለው ጊዜ ከአምስት እስከ 40 ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡

**Leaching**: የከርሰ ምድር ውሃ ብክለት

As water moves through soils or landfills, chemicals in the soil may dissolve in the water thereby contaminating the groundwater. This is called leaching.
ውሃ በአፈር ወይም በምድር ላይ በሚፈስበት ወቅት በአፈር ላይ የሚገኝን ኬሚካል በውስጡ ከትቶ በመስረግ የከርሰ ምድሩ ውሃ እንዲበከል ያደርጋል፡፡ ይህ ሂደት በውሃ አማካኝነት የሚከሰት የከርሰ ምድር ውሃ ብክለት ይባላል፡፡

**Media**: ከባቢያዊ ናሙና

Elements of a surrounding environment that can be sampled for contamination; usually soil, water, or air. Plants, as well as humans (when sampling blood, urine, etc) can also be considered media.
የብክለትን መጠን ለማወቅ ከአካባቢው ለናሙናነት የሚወሰዱ በአመዛኙ እንደ አፈር፣ ውሃ ወይም አየር ያሉ ቁሶች ከባቢያዊ ናሙና (ሚዲያ) ይባላሉ፡፡ እንስሳት እንዲሁም የሰው ልጅ (የደምና ሽንት ናሙና ሲሰጥ) እንደ ከባቢያዊ ናሙና ሊታዩ ይችላሉ፡፡

**Millennium Development Goals (MDGs)**: የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፡

A set of eight measurable goals agreed upon by world leaders following the United Nations Millennium Summit in 2000, to combat poverty,

hunger, disease, illiteracy, environmental degradation, and discrimination against women.
የአለም መሪዎች በመስከረም ወር እ.ኤ.አ 2000 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት የመሪዎች ስብሰባ ላይ ድህነት፣ረሃብና፣በሽታን፣መሃይምነትን፣የአካባቢ መራቆትንና በሴቶች ላይ የሚደርሱ አድሎዎችን ለማስቀረት ያጸደቁትና በባለ ስምንት የልማት ግቦች የሚለካ እቅድ ነው፡፡

## Morbidity፡ ታማሚነት

A morbidity rate for a certain illness is the number of people with that illness divided by the number of people in the population from which the illnesses were counted.
የአንድ የተወሰነ በሽታ የታማሚነት መጠን የሚሰላው በበሽታው የተጠቁትን ሰዎች ቁጥር ለአጠቃላይ በሽታው ለተገኘበት አካባቢ ነዋሪ ብዛት በማካፈል ነው፡፡

## Odor threshold፡ የጠረን መጠን

The lowest concentration of a chemical that can be smelled. Different chemicals have different odor thresholds. Also, some people can smell a chemical at lower concentrations than others can.
ሊሸተት የሚችል የኬሚካል ዝቅተኛ መጠን ነው፡፡ የተለያዩ ኬሚካሎች የተለያየ አይነት የጠረን መጠን አላቸው፡፡ በዚሁ ዓይነት አንዳንድ ሰዎች ዝቅተኛ መጠን ያላቸውን ኬሚካሎች እንኳን በማሽተት የሚለዩ ሲሆን አንዳንዶች ግን ይሄ ይሳናቸዋል፡፡

## Permeability፡ የማሳለፍ ደረጃ

The property of permitting liquids or gases to pass through. A highly permeable soil, such as sand, allows a liquid to pass through quickly. Clay has a low permeability.
ፈሳሽን ወይም ጋዝን የማሳለፍ ደረጃ፡፡ ከፍተኛ የማሳለፍ ደረጃ ያለው አፈር ለምሳሌ አሸዋ ፈሳሽ በውስጡ በፍጥነት እንዲያልፍ የማድረግ ሁኔታ አለው፡፡ ሸክላ ደግሞ በጣም ዝግ ብሎ ነው የሚያሳልፈው፡፡

## Persistence፡ ከረጅም ጊዜ መቆየት

The quality of remaining for a long period of time (such as in the environment or the body). Persistent chemicals (such as DDT and PCBs) are not easily broken down.
ለረጅም ጊዜ የመቆየት ወይም የመዝለቅ ደረጃ (ለምሳሌ በአካባቢ ላይ ወይንም በሰውነት ውስጥ) ማለት ነው፡፡ ቶሎ የማይጠፉ እንደ ዲዲቲ እና ፒሲቢ የመሳሰሉ ኬሚካሎች በቀላሉ የሚወድሙና የሚጠፉ አይደሉም፡፡

## Preliminary Site Assessment (PSA)፡ የመስክ ቅድመ ጥናት

A process makes to determine if a site contains hazardous waste and

its potential for harming the public health or environment. This process includes inspecting the site, sampling if needed, and taking physical measurements as appropriate.
መስኩ አደገኛ የሆነ ፍሳሽ መያዙንና ይህም ለነዋሪውና ለአካባቢው አደገኛነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለመለየት የሚደረግ የጥናት ሂደት ነው። ይህ ሂደት መስኩን የመቃኘት፣ ናሙና የመውሰድ እና እንደ አስፈላጊነቱም አካላዊ ምርመራ ማድረግን ያካትታል።

**Protocol**: **ዝርዝር አቅድ**

The detailed plan for conducting a scientific procedure. A protocol for measuring a chemical in soil, water or air describes the way in which samples should be collected and analyzed.
ዝርዝር እቅድ አንድን ሳይንሳዊ ሂደት ለማከናወን የሚሰራ ዝርዝር እቅድ ነው። ለምሳሌ በአፈር፣ በውሃ ወይም በአየር ውስጥ የሚገኝን የኬሚካል መጠን ለመለካት የሚሰራ ዝርዝር እቅድ ናሙናው እንዴት እንደሚሰበሰብና እንዴት እንደሚመረመር ያመላክታል።

**Remedial Investigation (RI)**: **የመታደጊያ ምርመራ**

An in-depth study (including sampling of air, soil, water and waste) of a contaminated site needing remediation to determine the nature and extent of contamination.
አንድን የተበከለን አካባቢ ለመታደግ የሚደረግ ዝርዝር ጥናት (የአየር፣ አፈር፣ ውሃ እና የተወገደ ፍሳሽን ወይም ጠጣር ነገርን ናሙና በመውሰድ ጭምር) ሲሆን፤ በዚህም የብክለቱን ይዘትና ስፋት ለመለየትና ለመወሰን ይቻላል።

**Remediation**: **መታደግ**

Correction or improvement of a problem, such as work that is done to clean up or stop the release of chemicals from a contaminated site.
አካባቢን ከብክለት የጸዳ ለማድረግ ወይንም የኬሚካል ልቀትን ለማስቀም የሚወሰድ የማስተካከያ እና የማሻሻያ መንገድ ነው።

**Risk management**: **የአደጋ ተጋላጭነት ቁጥጥር**

The process of deciding how and to what extent to reduce or eliminate risk factors by considering the risk assessment, engineering factors, social economic and political concerns.
የስጋት ቅኝትን፣ የምህንድስና አቅጣጫዎችን፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የስጋት ደረጃዎችን እንዴት እና እስከምን ድረስ ማስወገድ እንደሚቻል የሚወሰንበት አሰራር ነው።

**Site inspection**: **የመስክ ፍተሻ**

A Department of Health visit to a site to evaluate the likelihood of human

exposure to toxic chemicals and to do an exposure assessment.
በጤና መምሪያ አማካኝነት የሚደረግ የመስክ ጉብኝት ሆኖ፤ ዋና ዓላማውም በአካባቢው ያለው ሰው ለአደገኛ ኬሚካሎች ያለውን ተጋላጭነት ለመገምገምና የተጋላጭነት ደረጃ ምዘና የማድረጊያ የቁጥጥር ጥናት ነው።

**Target organ**፡ ተጠቂ የሰውነት አካል

An organ (such as the liver or kidney) that is specifically affected by a toxic chemical
በአደገኛ ኬሚካል የተጠቃው እንደ ጉበት ወይንም ኩላሊት ያለ የሰውነት አካል።

**Aforestation**: የደን ልማት

Creation of a forest on land that has not previously, at least in recent times, had a significant tree population
ከዚህ ቀደም በመሬቱ ላይ ያልነበረን ደን በማልማት የዛፎችን ቁጥር መጨመር።

# 5. የልማት ሙያዊ ሙዳየ ቃላት
## Glossary of development terms

**AID**: አርዳታ

The words "aid" and "assistance" in this publication refer only to flows which qualify as OFFICIAL DEVELOPMENT ASSISTANCE (ODA).
ይህ ቃል በተለይ በልማት ውስጥ የሚያመላክተው በይፋ የተደረገ የልማት እርዳታን ነው፡፡

**AID EFFECTIVENESS**: የአርዳታ ውጤታማነት

The efforts of the development community to improve the delivery of AID to maximize its impact on development
የእርዳታ ሁኔታው በልማት ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ የማድረግ የልማት ማህበረሰቡ ጥረት፡፡

**Alignment**: አርዳታን በተከጋሹ አገር ፍላጎት ጋር መጣጣም

Donor countries bring their support in line with the country's objectives and use local systems.
የለጋሽ አገራት እርዳታቸውን በተረጂዋ አገር መሰረታዊ ፍላጎትና ባላት የአሰራር ስርዓት ውስጥ መካተት ፡፡

**AMORTISATION**: ዋና ብድር

Repayments of principal on a LOAN. Does not include interest payments
የብድሩን ዋናውን ገንዘብ ብቻ መክፈል፡፡ ይህ የወለድ ክፍያን አይጨምርም፡፡

**BUSAN**: ቡሳን

Often referred to as the Fourth High-Level Forum on Aid Effectiveness, held from 29 November to 1 December 2011, in Busan, Korea
በእርዳታ ውጤታማነት ላይ የመከረው የአራተኛው ከፍተኛ ደረጃ ፎረም መጠሪያ ሲሆን፣ ስያሜውንም ያገኘው በቡሳን ኮሪያ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከኖቨምበር 29 እስከ ዲሴምበር 1፣2011 በመካሄዱ ነው፡፡

**Baseline**: የለውጥ መለኪያ መነሻ

State of the economic, social or environmental context, at a given time (generally at the beginning of the intervention), and from which changes will be measured.
በአንድ በተወሰነ ጊዜ የነበረ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የአካባቢ ጥበቃ ሁኔታ ሲሆን፣ ይሄም የሚያገለግለው ከርሱ ተነስቶ የተገኘውን ለውጥ ለመለካት ነው፡፡

**CLAIM**: ጥያቄ ማቅረብ

The entitlement of a creditor to repayment of a LOAN; by extension, the loan itself or the outstanding amount thereof
ያበዳሪው ወገን መብት ሆኖ ተበዳሪውን የብድሩን ዋናውን ገንዘብ ወይንም ወለዱን በረጅም ጊዜ እንዲከፍል ለማድረግ የሚያቀርበው ይፋዊ ጥያቄ ነው፡፡

## COMMITMENT: ቃል መግባት

A firm obligation expressed in writing and backed by the necessary funds, undertaken by an official donor to provide specified assistance to a recipient country or a multilateral organization.
አንድ ድርጅት በእርዳታ መልክ ይሄን አከናውናለሁ፤ ለሥራው የሚሆነውንም ይህን ያህል በጀት መድቤያለሁ ብሎ ለተለጋሹ አገር ወይም ከፍተኛ ተቋም በጽሁፍ የሚገልጽበት ሂደት ቃል መግባት ይባላል፡፡

## DECLARATION ON AID EFFECTIVENESS: የእርዳታ ውጤታማነት ድንጋጌ

The Third High-Level Forum on Aid Effectiveness in Accra, Ghana took stock of progress and built on the Paris Declaration to accelerate the pace of change. The AAA, adopted in Accra on 4 September 2008, reflects the international commitment to support the reforms needed to accelerate an effective use of development assistance and helps ensure the achievement of the MDGs by 2015.
በጋና አክራ በእርዳታ ውጤታማነት ላይ የተካሄደው ሦስተኛው ከፍተኛ ደረጃ ፎረም የፓሪሱን ስምምነት በማጠናከርና ሌሎች አዳዲስ እድገቶችን በማካተት ለውጥን የማቀላጠፍ ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡ ይሄው እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በመስከረም 4 ቀን 2008 የተደረገው የአክራው ድንጋጌ ተረጂ አገራት ተሃድሶ በማድረግ የልማት እርዳታዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተጠቅመው በ2015 ለማሳካት የያዙትን የሚሊኒየሙን የልማት ግብ እቅድ እንዲያሳኩ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ቁርጠኝነት እና እገዛ የጠየቀ ነው፡፡

## DISBURSEMENTS: ክፍፍል

Commitments to multilateral organizations are reported as the sum of: any disbursements in the year in question which have not previously been notified as commitments; and ii) expected disbursements in the following year.
ለዓለም አቀፍ ከፍተኛ ድርጅቶች የተገባ የፈንድ ቃል ሆኖ፤ 1ኛ ቀደም ብሎ ቃል ያልተገባ ነገር ግን በጥያቄ ቀርቦ በአመቱ የተከፈለ ማንኛውም ዓይነት ክፍያ፣ 2ኛ በሚቀጥለው ዓመት ይከፈላል ተብሎ የሚጠበቅ ክፍያ ማለት ነው፡፡

## Harmonization: ማቀናጀት

Donor countries co-ordinate their action, simplify procedures and share information to avoid duplication.
የልማት ሥራ ወይም የእርዳታ ድግግሞሽን ለማስቀረት የለጋሽ አገራት ሥራውን የማቀናጀት፣ የአሰራር ሂደቱን የማቅለልና የመረጃ መለዋወጫ መንገድ ነው፡፡

**LMICs**: ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራት

Lower middle-income countries, i.e. those with GNI per capita (Atlas basis) between USD 1 006 and USD 3 975 in 2010.
ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተብለው የተለዩት ጂ ኤን አይ በተባለው የመመደቢያ መስፈርት መሰረት እኤአ በ 2010 የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከ1006 እስከ 3975 የአሜሪካን ዶላር የሆኑ ናቸው፡፡

**LDCs**: በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮች

Least developed countries, a group established by the United Nations (UN). To be classified as LDCs, countries must fall below thresholds established for income, economic diversification and social development.
በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮች ዝርዝርን ለይቶ ያስቀመጠው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ነው፡፡ አገራት በዚህ ምድብ ውስጥ የተካተቱት ከተቀመጠው አመታዊ ገቢ፣ ካላቸው የኢኮኖሚ ስብጥር እና ማህበራዊ ልማት አንጻር ተገምግመው ነው፡፡

**Managing for results**: ውጤት ተኮር አመራር

Developing countries and donors focus on producing and measuring results.
በማደግ ላይ ያሉ አገራትና ለጋሾች ክንውናቸውና በዚያ ክንውን የተነሳም በተገኘው ውጤት ላይ ትኩረት ሲሰጡ፡፡

**Mutual accountability**: የጋራ ተጠያቂነት

Donor and developing country partners are accountable for development results to each other and to their electorates.
በማደግ ላይ ያሉ አገራትና ለጋሾች የልማት ውጤቶችን አስመልክቶ አንዳቸው ለአንዳቸው እንዲሁም ለመረጣቸው ህዝብ ተጠያቂነትን ያሰፍናሉ፡፡

**Ownership**: ባለቤትነት

Developing countries set their own strategies for development, improve their institutions and tackle corruption. In Accra (2008) it was widely recognized that "ownership" should also refer to the inclusion of a wide variety of country stakeholders in the process.
በማደግ ላይ ያሉ አገራት ከልማት ጋር በተያያዘ የራሳቸውን የልማት ስልት ይነድፋሉ፣ተቋማቶቻቸውን ያሻሽላሉ እንዲሁም ሙስናን ይዋጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ እኤአ በ2008 አክራ ላይ የልማት ሥራ ባለቤትነት የሚለው መንፈስ በየአገራቱ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን በልማት ሥራ ሂደት ውስጥ ማካተት እንደሚገባ በሰፊው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

**Other LICs**: ሌሎች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች

Other low-income countries; includes all non-LDCs with per capita gross national income (GNI) of USD 1 005 or less in 2010 (World Bank Atlas basis).
በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት አገራት ሁሉም በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አገራት ምድብ ውስጥ ያልተካተቱ አገራት ሲሆኑ የነፍስ ወከፍ ጥቅል አገራዊ ገቢያቸውም በአለም ባንክ ምደባ መሰረት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2010 1005 የአሜሪካ ዶላር እና ከዚያ በታች የሆነ ናቸው።

**PARTIALLY UNTIED AID**: አስፈካጊው ግዢ የሚካሄድባቸውን አገራት ለይቶ ያስቀመጠ እርዳታ

ODA for which the associated goods and services must be procured in the donor country or among a restricted group of other countries that must, however, include substantially all recipient countries.
የልማት እገዛ ሆኖ ለዚያው ልማት የሚውለው እቃና አገልግሎት ግን የግድ መገዛት ያለበት እርዳታውን ከሚሰጠው አገር ወይም ተመርጠው ከተለዩት በሌላ አገር ካሉ ቡድኖች መካከል ነው። ይሁን እንጂ ግዢው ተቀባይ አገሮችንም የግድ ማካተት አለበት።

**PARTNER COUNTRY**: አጋር ሀገር

Refers to countries that receive development assistance provided by other countries to support their own development
የራሱን አገር የልማት ሥራ ለማከናወን የልማት እርዳታ ተቀባይ የሆነው ሀገር አጋር ሀገር በመባል ይታወቃል።

**Securities of multilateral agencies**: የድንበር ተሻጋሪ ተቋማት ዋስትናዎች።

This covers the transactions of the private, non-bank and bank sector in bonds, debentures, etc. issued by MULTILATERAL AGENCIES
ከከፍተኛ ተቋማት ወደ ግል ተቋማት፣ የባንክ አገልግሎት የማይሰጡ ድርጅቶችና ወደ ባንኮች የሚደረግን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር የሚሸፍን የድንበር ተሻጋሪ አገራት የገንዘብ ደህንነት።

**Technical co-operation**: ቴክኒካዊ ትብብር

Includes both: i) GRANTS to nationals of aid-recipient countries receiving education or training at home or abroad; and ii) payments to consultants, advisers and similar personnel, as well as teachers and administrators serving in recipient countries
ይህ ትብብር አንደኛ በተረጂ አገር ለሚገኙ ሰዎች ለትምህርት ወይም ለስልጠና የሚደረግ እርዳታን፣ ሁለተኛ ለአማካሪዎች፣ ለኮንሰልታንቶችና ለመሳሰሉ ግለሰቦች እንዲሁም በተረጂው አገር ውስጥ በአስተማሪነትና በአስተዳደር ዘርፍ ለሚያገለግሉ የሚከፈል ወጪን የሚሸፍን ነው።

**Tied aid**: የተቀየደ እርዳታ

Official GRANTS or LOANS where procurement of the goods or services is limited to the donor country or to a group of countries, which does not include substantially all aid-recipient countries.
ይፋዊ የሆነ ብድር ወይም እርዳታ ሆኖ ለእርዳታ ሥራው የሚያስፈልጉ ማነቸውም እቃዎችም ሆኑ አገልግሎቶች ግን ተገዝተው የሚቀርቡት ከለጋሹ አገር ወይም ከለጋሽ አገሮች ቡድኖች ብቻ ነው፡፡ በዚህ የእርዳታ አይነት ግዢው ከተለጋሽ አገራት አይከናወንም፡፡

**TOTAL RECEIPTS**: ገቢ የሆነ አጠቃላይ እርዳታ

The inflow of resources to aid-recipient countries
ወደ አንድ አገር ገቢ የሆነ አጠቃላይ የእርዳታ ሃብት መጠን፡፡

**UNDISBURSED**: ያልተከፋፈለ ገንዘብ

Describes amounts committed but not yet spent
ቃል ተገብቶ ነገር ግን እስካሁን ገቢ ያልተደረገ ገንዘብ፡፡

**UNTIED AID**: ግዢው በቅድመ ሁኔታ ያልተገደበ

ODA for which the associated goods and services may be fully and freely procured in substantially all countries
የልማት እርዳታ ሆኖ ለእርዳታው ሥራ የሚያስፈልጉት እቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ከረጂውም ሆነ ከተረጂው አገር ሙሉ በሙሉና ከቁጥጥር ነጻ በሆነ መልኩ ሲፈጸም፡፡

**UMICs**: ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራት

Upper middle-income countries, i.e.those with GNI per capita (Atlas basis) between USD 3976 and USD 12275 in 2010
ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የእድገት መጠን መለኪያ መስፈርት መሰረት እኤአ በ2010 የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከ3976 እስከ 12275 የአሜሪካን ዶላር የሆኑ አገሮች፡፡

# 6. List of International Organizations work on the area of Health, Environment and Development

**Cervical Cancer Prevention**. In 1999, with support from the Bill & Melinda Gates Foundation, five international agencies launched a major new effort to prevent cervical cancer worldwide. This group of organizations, coordinated by the nonprofit group PATH, is working to clarify, promote, and implement strategies for preventing cervical cancer in developing countries.

**Centers for Disease Control and Prevention (CDC)** is a U.S. government agency whose mission is to promote health and quality of life by preventing and controlling disease, injury, and disability. It works throughout the United States and the world monitoring health, investigating health problems, conducting research, and implementing prevention strategies.

**Center for Reproductive Rights** is a nonprofit legal advocacy organization based in the United States dedicated to promoting and defending women's reproductive rights worldwide.

**Demographic and Health Surveys (DHS)** project is a global data collection effort funded by the U.S. Agency for International Development and carried out by ORC Macro and in-country organizations. These nationally representative household surveys collect data on demographic patterns, fertility, health, and nutrition for policy and program planning.

**Millennium Project.** The Millennium Project was commissioned by the United Nations Secretary-General in 2002 to develop a concrete action plan for the world to achieve the Millennium Development Goals. Its task forces include more than 250 experts worldwide from the public and private sectors.

**Population Council.** The Population Council conducts research worldwide to improve policies, programs, and products in three areas: HIV and AIDS; poverty, gender, and youth; and reproductive health. The Council has a Middle East program and regional office based in Cairo, and an Arabic section on its website.

**Population Reference Bureau** informs people around the world about population, health, and the environment, and empowers them to use that information to advance the well-being of current and future generations. PRB's International Programs aim to bridge the gap between research and policy on a wide range of topics including reproductive health, gender, global health priorities, population dynamics, the environment, and youth.

**Population Reports** is a quarterly journal published by the Johns Hopkins University Center for Communications Programs and supported by the

United States Agency for International Development that is designed to provide an accurate and authoritative overview of important developments in family planning and related health issues.

**Pan Arab Project for Family Health (PAPFfAM)** operates under the auspices of the League of Arab States and aims to enable Ministries of Health and other national health institutions in the Arab region to obtain timely and reliable information for formulating, implementing, monitoring, and evaluating family health and reproductive health policies and programs.

**Save the Children** is an international nonprofit organization founded in the aftermath of World War I that works to improve the lives of children in need and mobilizes lifesaving assistance to children in times of war, conflict, and natural disasters.

**Disease Control Priorities Project (DCPP)** assesses the major causes of ill-health in developing countries and produces evidence-based analysis and resource materials to inform health policymaking. In 2006, DCPP released the second edition of Disease Control Priorities in Developing Countries, published by the World Bank with input from some 600 public health and policy experts.

**Global Health Council** is a U.S.-based nonprofit membership organization comprising health-care professionals and organizations that include NGOs, foundations, corporations, government agencies, and academic institutions. GlobalHealthReporting.org is a project operated by the U.S.-based Kaiser Family Foundation with major support from the Bill & Melinda Gates Foundation, providing journalists and others with the latest information on HIV, tuberculosis, malaria, and other topics.

**Guttmacher Institute** is a U.S.-based nonprofit organization focused on sexual and reproductive health research, policy analysis, and public education.

**International Consortium for Emergency Contraception** was founded by seven internationally known organizations working in the field of family planning with a mission to expand access to emergency contraception worldwide but especially in developing countries.

**IPAS** is an international nonprofit organization that has worked for three decades to increase women's ability to exercise their sexual and reproductive rights and to reduce deaths and injuries of women from unsafe abortion.

**Multiple Indicator Cluster Surveys (MICS)** were developed by UNICEF in the mid-1990s to track progress toward the World Summit for Children goals. MICS surveys are now a major source of data for MDG monitoring, as well as the assessment of progress toward other international goals related to child health and HIV/AIDS.

# 7. References


ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፣አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ 1993

A Journalists Guide to Sexual and Reproductive Health in East Africa, Population Reference Bureau, 2011

Arthur Haupt and Thomas T. Kane, Population Reference Bureau's Population Handbook,

Cambridge University Press, 2003, Cambridge advanced learner's dictionary.

COM (2001) 295, Program of action for the mainstreaming of gender equality in community development co-operation. Annex I. 21 June 2001.

Development Co-operation, 2004, Regulation (EC)No.806/2004. EC

Donna Clifton, Toshiko Kaneda, and Lori Ashford, Family Planning Worldwide 2008

European Commission, (2004) Aid delivery methods: project cycle Management guidelines, Vol.1. March 2004

European Parliament and of the Council on Promoting Gender Equality in
http://esa.un.org/unpp
http://www.johannesburgsummit.org/ html/brochure/brochure12.pdf
May 2003.

Moser, C. O.N. (1993). Gender Planning and Development: Theory, Practice and Training. New York: Routledge, Chapman, and Hall. No 806/2004 on sustainable development. 26 Aug–4 Sep 2002

Participatory gender audit revised manual for auditors, Geneva. International Labour Office, Dec 2002.

PHE-Ethiopia Consortium, SCIP Project Toolkit,2014,Addis Ababa

PHE-Ethiopia Consortium, SCIP Project Toolkit,2014,Addis Ababa

Sexual and Reproductive Health Glossary70 www.prb.org Appx.

Sexual and Reproductive Health in MENA: A Guide for ReportersSexual and Reproductive Health in MENA: A Guide for Reporters Appendix 2 |

UNICEF, UNFPA, and the World Bank.UNICEF, UNICEF Global Database on Delivery Care.

United Nations, 2002 Brochure: Johannesburg Summit 2002. world summit

Washington, DC: Population Reference Bureau, 2008 Pan Arab Project for Family Health.ORC Macro Demographic and Health Surveys.World Health Organization, WHO Statistical Information System (WHOSIS Database). www.who.int/whosis/database/core/core_select.cfmWorld Health Organization, Maternal Mortality in 2005: Estimates Developed by WHO,

WHO, Glossary of globalization, trade and health terms www.childinfo.org/areas/deliverycare/countrydata.phpUNICEF, Multiple Indicator Cluster Surveys.United Nations Population Division, World Population Prospects: The 2006 Revision.

www.epa.gov/climatechange/glossary

www.epa.gov/climatechange/glossary.

www.prb.org/pdf/PopHandbook_Eng.pdfReproductive Health Outlook. www.rho.orgWhite Ribbon Alliance. www.whiteribbonalliance.org

**Designed & Printed by PHILMON PRESS**